# አዲስ ዘመን

እንድ

እሁድ 81ኛ ዓመት ቁጥር 240 ሚያዝያ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ






## "በግብርናው መስክ የተገኘውን ድል በኢንዱስትሪውም እንደግመዋለን"

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- እንደአገር በግብርናው መስክ የተገኘውን ድል በኢንዱስትሪውም ዘርፍ እንደግመዋለን ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ ታምርት የኢንዱስትሪ ንቅናቄ ትናንትና ሲካሄድ ግብርና ላይ ሥራ እንደምንችልና ሥራ እንደሚሳካልን አይተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዘርፉ የተከናወኑ ተግባራትን በማጠናከር በሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ ስንዴ

"በግብርናው መስክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# "የሠራዊቱ ወትሮ ዝግጁነት እጅግ አስደናቂ ነው"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

አዲስ አበባ፡- በምዕራብ ግንባር ተገኝቼ ያየሁት የሠራዊቱ ወትሮ ዝግጁነት እጅግ አስደናቂ ነው። ኢትዮጵያን ከማንም፣ በምንም ሁኔታና መቼም ሉዓላዊነቷን ለማስከበር ሁለንተናዊ ዝግጁነቱን ያረጋገጠ ሠራዊት ወሳኝ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስፈሩት መልዕክት እንደገለጹት ፤በምዕራብ ግንባር ተገኝቼ ያየሁት የሠራዊቱ ወትሮ ዝግጁነት እጅግ አስደናቂ ነው። ሁለንተናዊ ዝግጁነቱን ያረጋገጠ ሠራዊት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር ወሳኝ ነው።

ኢትዮጵያን ከማንም፣ በምንም ሁኔታና መቼም

" የሠራዊቱ ወትሮ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት እየተደረገ ነው

ኃይሉ ሣህለድንግል

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥለው ሐምሌ ወር ተግባራዊ መደረግ ለሚጀመረው የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ አሰራር ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ተጠቆመ።

የታለመ የነዳጅ ድጎማና የዋጋ ማሻሻያን በተመለከተ ለሚዲያ ባለሙያዎች በአዳማ ከተማ ሰሞኑን በተዘጋጀ መድረክ ላይ የኢፌዴሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሀመድ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንዳስታወቁት ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ በማህበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያሳድር በሚል የነዳጅ ዋጋ ማረጋጊያ ፈንድ ተቋቁሞ ሲሰራም ቆይቷል፤ ዓላማውም በዓለም የነዳጅ ገበያ ዋጋ ላይ በሚከሰተው ጭማሪ ምክንያት የሚያስፈልገውን ተጨማሪ ወጪ በመደጎም የነዳጅ ገበያ ዋጋን ማረጋጋት ነው።

የሀገሪቱን ወቅታዊ የማክሮ ኢኮኖሚና የሕብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የሀገር ውስጥ የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋና የዓለም አቀፉን ዋጋ በማጥበብ በኩል ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ከዓለም ገበያ ዋጋ ጋር የሚሄድ የዋጋ ማስተካከያ ሳይደረግ መቆየቱን ሚኒስትር ዴኤታው ጠቅሰው፤ በዚህ የተነሳም በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ እዳ በዋጋ ማረጋጊያ ፈንዱ ላይ ተከማችቶ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት ነዳጅ ከዓለም ገበያ ከተገዛበት ዋጋ ከግማሽ በታች ለገበያ እየቀረበ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህም ሁኔታ ከጎረቤት ሀገሮች የነዳጅ ዋጋ አንጻር ዝቅተኛ ሆኖ በመገኘቱ የነዳጅ ህገወጥ ግብይትና ኮንትሮባንድ እንዲስፋፋ ምክንያት እየሆነ እንደሚገኝም አስታውቀዋል።

በሥራ ላይ የቆየው ድጎማ ለሁሉም ተጠቃሚዎች ማለትም መደጎም ያለባቸውንና የሌለባቸውን ሳይለይ በእኩልነት ሲሰራበት እንደቆየ ጠቅሰው፣ ይህም ሁኔታ ኢፍትሃዊነት በስፋት ይታይበታል ብለዋል።

የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

አቶ ኦርዲን በድሪ

# የዘንድሮው የሸዋል ዒድ ኢትዮጵያዊ አንድነትን በሚያጠናክር መልኩ እንደሚከበር ተገለጸ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሐረር፡- የዘንድሮው የሸዋል ዒድ ኢትዮጵያዊ እህትማማችነትና ወንድማማችነትን በሚያጠናክር መልኩ እንደሚከበር የሐረሪ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ኦርዲን በድሪ ገለጹ።

ርዕሰ መስተዳድሩ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፣ በዓሉ እንደ ሀገር ያሉንን የፍቅር፣ የመቻቻል፣ የአብሮነትና ሌሎችም እሴቶቻችን በሚያጠናክር መልኩ ለማክበር ዝግጅት መጠናቀቁን አስታውቀዋል።

“ከሚያዝያ 30 እስከ ግንቦት 2 ቀን 2014ዓ.ም በክልሉ የሚከበረውን የሸዋል ዒድ “ከዒድ እስከ ዒድ” ወደ ሀገር ቤት የመምጣት ጥሪን ተቀብለው ከሚመጡ ዲያስፖራ እህትና ወንድሞቻችን ጋር የምናከብረው በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል” ብለዋል።

እንደ ርዕሰ መስተዳድሩ ገለጻ፣ የሸዋል ዒድ በሐረሪ ሕዝብ ዘንድ ከሚከበሩ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ በዓላት አንዱ ነው። የዘንድሮ የሸዋል ዒድ አከባበር በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅና የታቀደለትን ዓላማ እንዲያሳካ በስሩ በርካታ ንዑስ ኮሚቴዎችን የያዘ ዐቢይ ኮሚቴ ተቋቁሟል።

በዓሉ ሲከበር የክልሉን ኢኮኖሚ በሚያግዝ መልኩ እንዲሆን ይደረጋል ያሉት አቶ ኦርዲን፤ ከሚያዝያ 30 እስከ ግንቦት ሁለት ባሉት ቀናት በክልሉ የተሠሩ የልማት ሥራዎች እንደሚመረቁም ገልጸዋል።

በተጨማሪም፣ ዲያስፖራዎች በክልሉ ያሉ ቅርሶችና ሙዚየሞች እንዲጎበኙና በአግባቡ እንዲያውቋቸው ይደረጋል ብለዋል።

ሐረር ከተማ የሰላም፣ የመቻቻልና የፍቅር ከተማ ተብላ ዓለም አቀፍ ሽልማት ያገኘች ከተማ መሆኗን ጠቅሰው፤ የዲያስፖራው ማኅበረሰብ አባላትም የሰላም፣ የአብሮነትና የመቻቻል ከተማ ወደሆነችው የሐረር ከተማ እንዲመጡና የበዓሉ ታዳሚ እንዲሆኑ ዋና አስተዳዳሪው ጥሪ አቅርበዋል።

“በዓሉን ለመታደም የሚመጡ እንግዶቻችን የእንግድነት ስሜት ሳይሰማቸው ጥሩ ጊዜ እንዲያሳልፉ የማድረግ ኃላፊነት አለብን” ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የክልሉ ሕዝብ የተለመደው እንግዳ ተቀባይነቱን እንዲያሳይና ለበዓሉ በስኬት መጠናቀቅ የበኩሉን እንዲወጣ ጠይቀዋል።

የፀጥታና አካላትና ሌሎችም ማኅበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከምንጊዜውም በላይ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም አጽንኦት ሰጥተዋል።

በሐረር ከተማ ለሦስት ቀናት የሚከበረው የዘንድሮው የሸዋል ዒድ “ከዒድ እስከ ዒድ ወደ ሀገር ቤት” መርሐ ግብር አንዱ አካል ሲሆን ከሚያዝያ 30 እስከ ግንቦት ሁለት ባሉት ቀናት ኤግዚቢሽኖች፣ ሲምፖዚየሞች፣ ጉብኝቶችን ጨምሮ ሌሎችም ዝግጅቶች ይኖራሉ ተብሎ ይጠበቃል።

# ተቋሙ በባሌ ዞን ጎባና ሮቤ ከተሞች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶችና የህዝብ አብያተ መጻሕፍት 10 ሺህ መጻሕፍትን አበረከተ

**ዳንኤል ዘነበ**

ጎባ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት በባሌ ዞን ጎባና ሮቤ ከተሞች ለሚገኙ ትምህርት ቤቶችና የህዝብ አብያተ መጻሕፍት 10 ሺህ መጻሕፍትን አበረከተ ። ተቋሙ የለገሳቸው መጻሕፍትም በገንዘብ ሲተመኑ በአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር እንደሚገመቱ ተመልክቷል ።

"የንባብ ሳምንቱ መጽሐፍት የዕውቀት ምንጭ ጮራ፣ መዛግብት የታሪክ አሻራ "በሚል መሪ የትውልዱን የንባብ ባህል ለማሳደግ ዓላማ ያደረገው የንባብ ሳምንት ትናንት በባሌ ዞን ሮቤና ጎባ ከተሞች ተጀምሯል ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት ከኦሮሚያ ክልል የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት እና ከመዳ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የተዘጋጀው ሀገር አቀፍ የንባብ ሳምንት የምክክር መድረክ በባሌ ዞን ጎባ እና ሮቤ ከተሞች ሲካሄድ የብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ይኩኖአምላክ መዝገበ እንደተናገሩት ፤ ተቋሙ ከተመሠረተ 80 ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ፤ በእነዚህ ዓመታት ንባብን ባህል ያደረገ ትውልድ እንዲፈጠርና የንባብ ባህላችን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ እንዲቻል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማትና ከተለያዩ የባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር እየሰራ ይገኛል ።

በሀገር አቀፍ ደረጃ የንባብ ባህልን ለማሳደግና በመረጃ የዳበረ ማህበረሰብ ለመፍጠር የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው ፤ ይሄንኑ መሠረት በማድረግም በባሌ ዞን ጎባና ሮቤ ከተሞች በአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ዋጋ የሚገመቱ 10 ሺህ መጽሐፍትን



አበርክቷል ብለዋል ።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ ፤ በተቋሙ አጠቃላይ መጽሐፍቱ ለ16 አብያተ መጽሐፍት የተበረከተ ሲሆን ፤ ከዚህ መካከል 13 በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ አብያተ መጽሐፍት ፣ ሁለቱ ደግሞ በጎባና ሮቤ ለሚገኙ የህዝብ አብያተመጻሕፍት እንዲሁም አንዱ ደግሞ ለሮቤ ማረሚያ ቤት ውስጥ ለሚገኝ አብያተ መጽሐፍ የተበረከተ ነው ።

የጎባ ከተማ ከንቲባ አቶ ተሻለ ዲሳሳ በበኩላቸው ፤የንባብ ባህል ማደበሪያ መድረኮች ማህበረሰብ ተኮር የንባብ ባህል በየደረጃው እንዲዳብር ፤ የስነ ፅሁፍ ባለሙያዎች እንዲሁም የዘርፉ ምሁራን ያላቸውን እውቀት ልምድ እና ተሞክሮ ለተተኪው ትውልድ እንዲያስተላልፉ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ያስችላሉ ብለዋል ። በከተማችን ብሎ በሀገራችን የንባብ ባህልን እንዲዳብር ከማድረግ በተጓዳኝ ትውልዱ ቋንቋውን፣ ባህላቸውን ፣ታሪካቸውን፣ ዕውቀታቸውን፣ ልምዳቸውንና ኢኮኖሚያቸውን አዳብረው ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚረዳ ወሳኝ መንገድ መሆኑን ተናግረዋል ።

በባሌ ዞን ጎባ እና ሮቤ ከተሞች እየተካሄደ የሚገኘውን ሀገር አቀፍ የንባብ ሳምንት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት ከኦሮሚያ ክልል የባሌ ዞን ባህልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት እና ከመደ ወላቡ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የተዘጋጀው ነው ። ለአራት ቀናት በሚቆየው የንባብ ሳምንት ዝግጅት ላይ የመጻሕፍት አውደራዕይ፣ ሽያጭና የንባብ መርሐ ግብር ተካቷል። በዝግጅቱ ላይ መጽሐፍ አታሚዎች፣ አሳታሚዎች፣ ደራሲያን፣ የመጻሕፍት አከፋፋዮችና በንባብ ላይ የሚሰሩ የመንግሥትና የግል ተቋማት እየተሳተፉ ይገኛል ። ከሚያዚያ 29 እስከ ግንቦት 2 ቀን 2014ዓ.ም በሚቆየው የንባብ ሳምንት አንባቢያን፣ጸሐፊዎች፣ ተማሪዎችና ደራሲያን እንደሚገኙ ይጠበቃል።

# ሚዲያዎች በአገራዊ ምክክሩ ላይ ሊያበረክቱ ስለሚገባቸው አስተዋጽኦ ቀድመው እንዲዘጋጁ ተጠየቀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ሚዲያዎች በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ሊያበረክቱ ስለሚገባቸው አስተዋፅኦ ከወዲሁ አበክረው እንዲያስቡ ተጠየቀ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ እንደገለፁት፤ ኃላፊነት የማይሰማቸው አካላት ማህበራዊ የትስስር ገፆችን ተጠቅመው ህብረተሰቡን ሊያወናብዱ የሚችሉበትና አፍራሽ መልዕክት ሊያስተላልፉ የሚችሉበት ዕድል ሰፊ በመሆኑ ሚዲያዎች በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ሊያበረክቱ ስለሚገባቸው አስተዋፅኦ ከወዲሁ አበክረው ሊያስቡ ይገባል።

በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ማህበራዊ የትስስር ገፆች አወንታዊም ሆነ አሉታዊም ሚና ሊኖራቸው ይችላል። ይህን ታሳቢ በማድረግ መደበኛ መገናኛ ብዙሃን ኃላፊነት በጎደላቸው አካላት ሊነዙ የሚችሉ አሉባልታዎችንና መልዕክቶችን መመከት መቻል አለባቸው። ለዚህም ተዓማኒነታቸውን ገንብተው በፍጥነት ወደ ሕዝብ መረጃ የሚደርሱበትን መንገድ ሊያስቡ ይገባል ሲሉ መክረዋል።

በአዳራሽ ውስጥ ተሰባስበው ከሚመካከሩ ዜጎች ባሻገር አብዛኛው የሀገራዊ ምክክሩ መድረክ ሚዲያ ነው። ሚዲያዎች ታዓማኒነትን ገንብተውና ፈጥነው መረጃ የሚያቀብሉ በማድረግ ቀውስን እየፈጠረ ሰውን የሚያሸብረውን የማህበራዊ ትስስር ገጽ ማዳከም ይቻላል። ይህም ለሀገራዊ ምክክሩ በእጅጉ ይጠቅማል ብለዋል።

ምንም እንኳን አገራዊ ምክክሩ አካታች ቢሆንም በየአዳራሹ ተሰብስቦ መምከር የሚችለው ዜጋ ውስን ስለሚሆን ይህንን ክፍተት ለመሙላት ሚዲያ ትልቅ ኃላፊነት ይኖርበታል።

ታማኝ መረጃዎችን ለማውጣት ጊዜ ይፈልጋል፤ ጊዜው ሲሄድ ደግሞ ታማኝ መረጃዎች ዋጋቸውን አጥተው ሕዝብ ጋር ይደርሳሉ ያሉት ፕሮፌሰር አድማሱ፤ ፍጥነቱም ጥንቃቄውም እንዲኖር ደግሞ ሚዲያው በሰው ኃይልና በቴክኖሎጂ የተሟላ ሊሆን ይገባል።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደሚሉት፤ በአሁኑ ወቅት መገናኛ ብዙሃን በዚህ መጣ የማይባል የመዋጊያና የማጥቂያ ስልት ሆነዋል። የአንድ ሀገር ውጊያ በጦር መሣሪያና በጦር ሠራዊት ሲሆን አካላዊ ስለሚሆን ለመከላከልም ለማጥቃትም ምቹ ነው። ሚዲያን የተመለከትን እንደሆነ ግን በትንሽ ሰከንዶች



ፎቶ፡ ከደክመ ጌት

ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ

ውስጥ የእያንዳንዱ ቤት ውስጥ መድረስ ስለሚችል ከባዱ የውጊያ ሜዳ ሆኖ ይገኛል። ይህንን የውጊያ ስልት ለመቋቋም ሚዲያዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ ተነቃቅተው መሥራት እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ ልክ እንደ ፍርድ ቤት ሥርዓት ሁሉ ሊዘገብበት የሚገባ አካሄድና ሥርዓት ስለሚኖረው በዚህ ዙሪያም ከሚመለከታቸው ጋር ተባብሮና ተቀናጅቶ መሥራት እንደሚገባ ፕሮፌሰር አድማሱ አሳስበዋል።

ፕሮፌሰር አድማሱ እንደገለጹት፤ ሀገርን በጥሩ ሁኔታ ከሚገነቡ ነገሮች ሀገራዊ ምክክር አንዱ ቢሆንም ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ግን ሁሉም አካል የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ ነው። መገናኛ ብዙሃን በሀገር ሰላምና ዕድገት ላይ የሚጫወቱትን ሚና በሀገራዊ ምክክሩ ወቅትም ተግተው በመሥራት ሊፈጠሩ የሚችሉ ክፍተቶችን መዝጋት እንደሚኖርባቸው አስገንዝበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላም እና የተረጋጋ ኢኮኖሚ- ጊዜ የማይሰጡ የጋራ የቤት ስራዎቻችን!

አገራችን አሁን የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ እጅግ ፈታኝ ስለመሆኑ ምስክር የሚያሻው ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም እያንዳንዱ ዜጋ ያለበትን ሁኔታ የሚያውቀው ነውና። በአሁኑ ወቅት በአንድ በኩል የኑሮ ውድነት የእያንዳንዱን ዜጋ በር ያንኳኳበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሰላም ሁኔታ ወዴት ይዞን ይሄዳል የሚለው ስጋት ከእያንዳንዱ ዜጋ ልብ ውስጥ የሚመላለስበት ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡

አገራችንን ወደብልጽግና ለመውሰድ በቅድሚያ ሰላም ወሳኝ ነው። ሰላም በሌለበት ሁኔታ እድገት ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም። በመሆኑም በቅድሚያ ዘላቂ ሰላም የሚረጋገጥበትን መንገድ መፈለግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

አሁን ባለው ሁኔታ በአንድ በኩል በአሸባሪው ሕወሓት የተከፈተውና ከአንድ አመት በላይ የዘለቀው ጦርነት ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በሸኔ ላይ የተጀመረውን እርምጃ በማፋጠን ህብረተሰቡ ሰላም የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ሕወሓት ካለፉት አርባ አመታት ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ ደባ ሲፈጽም የኖረና ኢትዮጵያን የማፈራረስ ኣላማ ይዞ ሲሰራ የቆየ ቡድን መሆኑ ቢታወቅም፤ ባለፈው አንድ አመት ተኩል ግን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በከፈተው ቀጥተኛ ጦርነት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎችን ለሞት፣ በሚሊየኖች የሚቆጠሩትን ለመፈናቀል እንዲሁም በብዙ ቢሊየን የሚቆጠር የአገር ሃብት እንዲወድም በማድረግ የኢትዮጵያን ህልውና ተፈታትኗል።

በዚህ ጊዜ ውስጥ በሰው ልጆች ላይ ከደረሰው ኢሰብአዊ ኪሳራ ባሻገር የባከነው ሃብትና ንብረት ለልማት ቢውል አገራችንን አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያራምድ ስለመሆኑ ማንም የማይክደው እውነታ ነው። ጦርነት የእድገት ጠንቅ ነው። ጦርነት የሚያስከፍለው መስዋዕትነት በገንዘብ አይተመንም። ይህንን ያህል ዋጋ የሚያስከፍል ክፉ ተግባርን የሙጥኝ ማለት ደግሞ ከጥፋት ውጭ የሚያመጣው አንዳችም ጠቀሜታ አይኖረውም። ሕወሓት በዚህ ጊዜ ውስጥ ጦርነትን የሙጥኝ በማለቱ በአንድ በኩል የትግራይን ህዝብ ለከፍተኛ ስቃይና እንግልት ከመዳረጉም በላይ መከራውን ለአማራና ለአፋር ህዝብም አትርፏል። ከዚህም አልፎ መላ ኢትዮጵያውያን የችግሩ ገፈት ቀማሽ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ ችግሩን የከፋ የሚያደርገው ቡድኑ ዛሬም ቢሆን ከዚህ ተምሮ ለሰላም የሚዘረጉ እጆችን እየረገጠ ጦርነትን ብቸኛ አማራጭ አድርጎ የሚጓዝ መሆኑ ነው። ይህ ቡድን ከደረሰበት ኪሳራና እሱም ካደረሰው ጥፋት ሳይማር ጦርነት ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ ይሰብካል። ባገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የጦርነት ነጋሪቶችን እየጎሰመ ወጣቶችን ለጦርነት የመቀስቀስ ተግባሩን ተያይዞታል። የትግራይ እናቶችን ባዶ ቤት ለማስቀረት ወጣቶችን ወደጦርነት ለመመልመል ዛሬም አላረፈም፡፡

በአንጻሩ መንግስት ለሰላም በርካታ እድሎችን ሲሰጥ ቆይቷል። ገና ከመጀመርያው ጀምሮ ሕወሓት ወደጦርነት እንዳይገባ የተጓዘበት ርቀት ብዙ ነበር። የመንግስት ትዕግስት በብዙዎች ዘንድ ልፍስፍስ እና ጦርነት የይችል አድርገው እስኪቆጥሩት ድረስ ብዙ ርቀት የሄደ ነበር። በሕወሓት ተገፍቶ ወደህልውና ዘመቻው ከገባ በኋላም ቢሆን ለሰላም እድሎችን ከመስጠት አልተቆጠበም። በመጀመርያው የህልውና ዘመቻ ወቅት የሕወሓት አመራሮች ለሰላም ሲሉ ጦርነቱን አቁመው ወደሰላም እንዲመለሱ በርካታ ጥሪዎችን አድርጓል። ከዚያም አልፎ የተኩስ አቁም በማድረግ ጦሩን ከትግራይ ክልል አስወጥቷል፡፡

ነገር ግን ሕወሓት ይህንን እድል እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ለዳግም ወረራ እንዲዘጋጅ አደረገው። በዚህም የአማራና አፋር አካባቢዎችን በመውረር ጅምላ ጭፍጨፋዎችን አካሄደ፤ በርካታ መሰረተ ልማቶችን አወደመ፣ ህብረተሰቡንም አፈናቀለ።

ከሁሉ በላይ የሕወሓትን ድርጊት አስከፊ የሚያደርገው ደግሞ በአንድ በኩል ህዝቡን ለጦርነት እየዳረገ በሌላ ጎኑ ደግሞ ዛሬም ህዝቡን ለከፋ ድህነት እየዳረገ መሆኑ ነው። በርካታ የትግራይ ህዝብ ቀደም ሲል ሕወሓት በስልጣን ላይ በነበረበትም ወቅት ቢሆን የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ነበር። ዛሬም ሕወሓት ይህንን ህዝብ ከዚህ የድህነት አረንቋ ማስወጣት ሲገባው ለሌላ ልመና እየዳረገው ነው። ዘሬ የትግራይ ደሃ ህብረተሰብ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል መካከለኛ ገቢ የነበራቸው ዜጎች ጭምር የሴፍቲኔት ጠባቂ እንዲሆኑ አድርጓል። በአጠቃላይ ሕወሓት ከጦርነቱ ያተረፈው ይህንን የቁልቁለት ጉዞ ብቻ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ህዝብ ከሚነሱ ጥያቄዎች ውስጥ ዋነኞቹ የሰላምና የኢኮኖሚ ጥያቄዎች ናቸው። ሰላም ከሌለ ሰርቶ መግባትም ሆነ ተዘዋውሮ በልቶ ማደር አይቻልም። በመሆኑም በሃገራችን ዘላቂ ሰላምን ማስፈን የግድ ነው። በዚህ ውስጥ ደግሞ በተለይ ከሕወሓት ጋር የሚደረገው ጦርነት መቋጫ ሊያገኝ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል በአሁኑ ወቅት በጦርነቱም ሆነ በዓለም ላይ በተከሰተው የሰላም ቀውስ የተነሳ የዋጋ ንረት እና የኑሮ ውድነቱ እያንዳንዱን ቤት በር እያንኳኳ ነው። አሁን በልቶ ማደር ጭምር ፈተና እየሆነ ያለበት ሁኔታ እንዳለ ብዙዎች ይናገራሉ። ይህ ሁኔታ በአጭሩ ካልተቀጨና መፍትሄ ካልተበጀለት ደግሞ ህልውናችን ትልቅ ፈተና ሊገጥመው ይችላል። በመሆኑም በኢኮኖሚው ጉዳይ ላይ መንግስት የጀመረውን ኢኮኖሚውን የማረጋጋት ተግባር በማጠናከር ዘላቂ መፍትሄ የሚገኝበት ሁኔታ ላይ መስራት አለበት፡፡

በሌላ በኩል የንግዱ ማህበረሰብም ሆነ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት መንግስት የሚወስዳቸው እርምጃዎች በመከታተልና ከመንግስት ጎን በመቆም የጋራ ችግሩን በጋራ ለመፍታት ጥረት ማድረግ የግድ ነው። በተለይ የንግዱ ማህበረሰብ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ከንግዳችን የምናተርፈውን ብቻ ሳይሆን እንደ አገር ለሌሎችም ሚዛናዊ የሆነ አገልግሎት የምንሰጥበትን መንገድ መከተል እንዳለብን መዘንጋት የለብንም። ይህ ሲሆን ሁሉም ዜጋ በሰላም መኖር ይችላል፡፡


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## ኢትዮጵያን ለማዳን ሁሉም የሠላም አማራጭ ሊተገበሩ ይገባል!

በእምነት

ያለፈው ሳምንት እንደ አገር ብዙ ነገሮችን ያየንበት ያሳለፍንበት ብዙ ደስታዎች የኖሩ ቢሆንም በእኩይ ተግባራቸው የሰዎችን ደስታ ለማጠልሸት በሚጥሩ ሀይሎችም እዚህም እዚያም ችግሮች ሲንጸባረቁ ያለፉበት ሳምንት ነበር፡፡

እነዚህ ነገሮች ሁሉ ታዲያ እኛን እንደ አገር እንዳንቆም ከማድረጋቸውም በላይ ለጥፋት ለሚፈልጉን ሀይሎች አመቻችቶ የሚሰጠንም እንደሆነ ያስተዋለ ያለ እስከማይመስል ድረስ ኣላስፈላጊ ትርምስ ውስጥ እንድናልፍ ተገደንም ነበር፡፡ ነገር ግን ችግር ለመፍጠር የማይቦዝኑ ተላላኪዎች የመኖራቸውን ያህል በዛው ልክ ደግሞ የአገራቸው ሁኔታ የሚያሳስባቸው ህዝባቸው በሰላም ወጥቶ እንዲገባ የሚያስቡ በጠቅላላው ቅን ኢትዮጵያውያን ነገሩ ከስሩ እንዲደርቅ የራሳቸውን ሚና ተወጥተዋል፡፡ እኩይ ተግባር ፈጻሚዎቹን የምናወግዘውን ያህል እነዚህንም ሀይላት ማመስገን እንደሚገባ ደግሞ ልብ ማለት ያስፈልጋል፡፡

ያም አለ ይህ ግን አሁን አገራችን ሰላም ትፈልጋለች እዚህም እዚያም በጸብ አጫሪዎች እየተለኮሶ ያሉ እሳቶች ህዝቡን ለምሬት የአገርንም ኢኮኖሚ በማሽመድመድ ከፍተኛ ችግር እየፈጠሩ ነው፡፡ በመሆኑ አሁን ለአገራችን በምድር ላይ አሉ የተባሉ የሰላም አማራጮችን ሁሉ መጠቀም ደግሞ የግድ የሚለን ወቅት ላይ እንደሆንን ይሰማኛል፡፡

ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር ከላይ እንዳልኩት በዓለም ላይ አሉ የሚባሉ የሠላም አማራጮች አገራችንን እስከ ታደጉልን ድረስ ብንቀበላቸው ጥሩ ነው፡፡ እዚህ ላይ አጥፊዎችን ማጥፋት መረበሽ እንኳን የሚችሉት አገር ሲኖር መሆኑን ተገንዝበው ሁሉንም የሰላም አማራጮች ባይፈልጉም እንኳን እየጎመዘዛቸውም ቢሆን መቀበል አለባቸው እላለሁ። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች አንድ ቀን ልብ አግኝተው የተመለሱ እለት ዞሮ ዞሮ መግቢያቸው እምዬ አገራቸው በመሆኗ፡፡

እዚህ ላይ ምናልባት ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር ካለችበት ችግር ለማውጣት የሚመጣው የሠላም መፍትሄና የሠላም አማራጭ ከግል ፍላጎትና አቋም አንጻር ላይዋጥላቸው፣ ሊያማቸው፣ ሊጎመዝዛቸው ይችላል። ነገር ግን ኢትዮጵያን የሚያድን እስከሆነ ድረስ እየጎመዘዘም ቢሆን መቀበል ይገባል፡፡

ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር የምናመጣው የሠላም መፍትሄና የሠላም አማራጭ ከግል ፍላጎትና አቋም አንጻር ላይዋጥልን፣ ሊያመንና ሊጎመዝዘን ቢችልም ኢትዮጵያን የሚያድንና ህዝቡን ወደ ፊት የሚያሻግር እስከሆነ ድረስ መቀበል ያለብን እውነት ሊኖር እንደሚችል ከወዲሁ መረዳት ያስፈልጋል።

**ኢትዮጵያን ወደ ፊት ለማሻገር የምናመጣው የሠላም መፍትሄና የሠላም አማራጭ ከግል ፍላጎትና አቋም አንጻር ላይዋጥልን፣ ሲያመንና ሲጎመዝዘን ቢችልም ኢትዮጵያን የሚያድንና ህዝቡን ወደ ፊት የሚያሻግር እስከሆነ ድረስ መቀበል ያለብን እውነት ሲኖር እንደሚችል ከወዲሁ መረዳት ያስፈልጋል**

ኢትዮጵያውያን ሠላም እንፈልጋለን። የሠላም እጦት መላውን ኢትዮጵያዊ አንገሽግሾታል። በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ጽንፍ በሚከሰቱ ግጭቶች በርካታ የማህበረሰብ ክፍል እየተማረሩ እየተጎዱ ከቤት ንብረታቸው በግፍ እየተሰደዱና ላላስፈላጊ እንግልት እየተዳረጉ ነው። ይህ ጉዳይ አሁን ላይ በቃ ካልተባለ መቼም ሊያበቃ ካለመቻሉም በላይ እንደ አገር ስለመቀጠላችን ራሱ መገመት ከባድ ነው።

ከዚህ አንጻር በየትኛውም ደረጃ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎች በእነርሱ እምነት ኢትዮጵያን ወደ ፊት ያሻግራል ብለው የሚያምኑበትን የሠላም እቅድና አማራጭ ይዘው ቢቀርቡ፣ በየትኛውም ሁኔታ ሠላም እንዲሰፍን እንፈልጋለን የሚሉ ኢትዮጵያውያንም አጀንዳ እየሰጡ ከሚያባሏቸው መሰሪዎች ራሳቸውን ቢጠብቁ ወጣቱም በስሜት ሳይሆን በአስተዋይነት እያንዳንዱ እርምጃው አገር ላይ ምን እንደሚያስከትል በተረዳ መንገድ ቢጓዝ በጠቅላላው አስተዋይ አርቆ አሳቢ በመሆን በብልሃት ብንጓዝ ከገባንበት ችግር ለመውጣት ቀላል ይሆናል የሚል ግምት አለኝ፡፡

አሁን አገራችን ለገባችበት ችግር በትግራይ ክልል በኩል የተነሳው ጦርነት እንደ ምክንያት ይገለጻል፤ ነገር ግን የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ ኢትዮጵያ እንደ አገር እዚህ እንድትደርስ ጉልህ አበርክቶ ያለው ህዝብ መሆኑን መዘንጋት አይገባም፡፡ ይህ ጉልህ አበርክቶአቸውን እንዲቀጥል፤ ኢትዮጵያን ወደፊት ለማሻገር በሚደረገው ርብርብ ውስጥ የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት ግን ከሁላችንም የሚጠበቅ ከባድ የቤት ስራም ሆኖ ይታየኛል፡፡

እንደ ዜጋ የሽብር ቡድኑ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የተጎዱ አካባቢዎች በተለይ አፋርና አማራ አካባቢዎች እንዲሁም መላው ኢትዮጵያ ሠላም እንዲሆን እፈልጋለሁ፡፡ ያ ሠላም እንዴት መምጣት አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ግን ሁላችንም የራሳችንን ጠጠር መወርወር እንዳለብንም ይሰማኛል፡፡ በመሆኑም ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት መወያየትና መመካከር ይኖርባቸዋልም እላለሁ።

ይህንን ማድረግ ካልቻልን ግን ኢትዮጵያን እንወዳለን ማለት አንችልም፤ ይህን ጉዳይ ሁሉም ማህበረሰብና ፖለቲከኞች ሊረዱት ይገባል።በኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከታቸው ኢትዮጵያውያን ብቻ ናቸው።ኢትዮጵያን አልፈልግም የሚልን አካል ኢትዮጵያን ወደ ፊት እንዴት እናሻግራት በሚል ድርድርና ምክክር ወይም ውይይት ውስጥ ይካተት የሚል አቋም የለኝም።ምክንያቱም ጉዳዩ የኢትዮጵያውያን ስለሆነ።


ሕወሓት ጦርነትን የሙጥኝ በማለቱ የትግራይን ህዝብ ለከፍተኛ ስቃይና እንግልት ከመዳረጉም በላይ መከራውን ለአማራና ለአፋር ህዝብም አትርፏል። ከዚህም አልፎ መላ ኢትዮጵያውያን የችግሩ ገፈት ቀማሽ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ ችግሩን የከፋ የሚያደርገው ቡድኑ ዛሬም ቢሆን ከዚህ ተምሮ ለሰላም የሚዘረጉ እጆችን እየረገጠ ጦርነትን ብቸኛ አማራጭ አድርጎ የሚጓዝ መሆኑ ነው። ይህ ቡድን ከደረሰበት ኪሳራና እሱም ካደረሰው ጥፋት ሳይማር ጦርነት ብቸኛ አማራጭ እንደሆነ ይሰብካል። ባገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ የጦርነት ነጋሪቶችን እየጎሰመ ወጣቶችን ለጦርነት የመቀስቀስ ተግባሩን ተያይዞታል። የትግራይ እናቶችን ባዶ ቤት ለማስቀረት ወጣቶችን ወደጦርነት ለመመልመል ዛሬም አላረፈም፡፡

"በጥባጭ ካለ ማን በሰላም ይጠጣል" እንደሚባው ይህ ቡድን በመኖሩ መላ ኢትዮጵውያን ሰላም እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል። የዚህ ቡድን በሽታ እንደካንሰር በሁሉም የሃገሪቱ ክፍሎች ተሰራጭቶ የሰላም መደፍረስ መንስኤ ሆኗል። በመሆኑም ከዚህ አካባቢ ያለውን የሰላም ችግር ማጥራት ለዘላቂ መፍትሄ ወሳኝ ነው፡፡

ሕወሓት በግልጽ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦልም ድረስ እገባለሁ የሚሉ አመራሮች ያሉበት እንደመሆኑ፤ መርዝ ቀማሚዎችን ባለ መድኃኒት አድርጎ መቀበል ስህተትም ስለሚሆን ይህ በቅጡ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ይመስለኛል።በሌላ በኩል ግን አገራችንን ለማዳን በዓለም ላይ ያሉ የሰላም አማራጮችን ሁሉ በመጠቀማችን እናተርፍ ይሆናል እንጂ አንጎዳም።

ዜና



# ግንባታው የተንተተው አዲሱ የአባይ ድልድይ ግንባታ ፕሮጀክት አፈጻጸም 61 ነጥብ 5 በመቶ ደረሰ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኮቪድ-19 ወረርሽኝና አሸባሪው ህወሓት በከፈተው ጦርነት ምክንያት መስተጓጎል ተፈጥሮበት ግንባታው የዘገየው አዲሱ የአባይ ድልድይ ፕሮጀክት አፈጻጸም 61 ነጥብ 5 በመቶ መድረሱ ተገለጸ።

የድልድዩ ግንባታ ፕሮጀክት ምክትል ተጠሪ ኢንጂነር ፍቅረስላሴ ወርቁ ድልድዩ፣ በአንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የሚገነባው የአባይ ድልድይ 380 ሜትር ርዝመትና 43 ሜትር የጎን ስፋት ያለው መሆኑን አብራርተዋል።

ድልድዩ በአንድ ጊዜ ስድስት ተሽከርካሪዎችን ማስተላለፍ የሚችል ባለሁለት አካፋይ ያለውና አምስት ሜትር የሳይክልና የእግረኞች መንገድ ማካተቱን እንዲሁም የትራፊክ ምልክቶች፣ የድልድይ ላይ መብራቶች፣ የተሽከርካሪ መውጫና ሌሎች የኮንክሪት መዋቅሮች መያዙንም ተናግረዋል።

በ2011 ዓ.ም የተጀመረው ፕሮጀክት በ2013 ዓ.ም መጨረሻ መጠናቀቅ የነበረበት ቢሆንም፣ እስካሁን ያለው የግንባታ አፈጻጸም 61 ነጥብ 5 በመቶ ብቻ መሆኑን ገልጸዋል።

ለዚህም የኮቪድ-19 ወረርሽኝና በጦርነት ምክንያት በግንባታ ግብዓት አቅርቦት ላይ ጫና በመፍጠሩ ፕሮጀክቱን በተባለው ጊዜ ማጠናቀቅ አለመቻሉን ነው የተናገሩት።

የግብዓት አቅርቦት በሚፈለገው መጠን ከተሟላ ፕሮጀክቱን በ2015 ዓ.ም ለማጠናቀቅ እቅድ መያዙንና ለዚህም አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግ መጠየቃቸውን ኢዜአ ዘግቧል።በአባይ ወንዝ ላይ የሚገነባው አዲሱ የአባይ ወንዝ ድልድይ አፈጻጸም 61 ነጥብ 5 በመቶ ደርሷል

ኮቪድ 19፣ የወሰን ማስከበር ችግሮች እና አንዳንድ የጸጥታ ችግሮች ምክንያት የጊዜ ማሻሻያዎችን ማድረግ አስፈልጓል።በዚህም መሰረት መስከረም 2015 እንዲጠናቀቅ የጊዜ ማሻሻያ መደረጉን ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት ከአቅሙ በላይ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኘውን ነባሩን የአባይ ወንዝ ድልድይ ላይ ይደርስ የነበረውን የትራፊክ መጨናነቅና ጫና ይቀንሳል። የባህርዳር ከተማ እድገት እና ውበት የሚመጥን ደረጃውን የጠበቀ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ እንድትሆን ይረዳልም ብለዋል።

ድልድዩ ከሀገራዊ ፋይዳውም አልፎ ከሱዳን ጋር የሚያገናኝ በመሆኑ የሁለቱን ሀገራት የንግድና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ይበልጥ እንደሚያስተሳስርም ተመላክቷል።

## “የሠራዊቱ ወትሮ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሉዓላዊነቷን ለማስከበር፤ ሁለንተናዊ ዝግጁነቱን ያረጋገጠ ሠራዊት ወሳኝ ነው፤ በምዕራብ ግንባር ያየነውም ይህን ነው ሲሉም ገልጸዋል።

የሰራዊቱ የጀግንነት ምስጢር ድል የሚፈጥር መሆኑ፣ ከመሬት በላይ ለትውልድ የሚተላለፍ ስም ተክሎ ሞትን ማሸነፉ፣ ለድንገተኛ ክስተት የማይበገር፣ ፍላጎቱን ለዓላማ ያስገዛ መሆኑን አንስተዋል።

የነጻነትን ዋጋ ማወቁ ፣ ጨለማን ወደ ብርሀን የሚቀይር ጉልበት ስላለው እና በልማትና ጥፋት መካከል የማይፈርስ ጠንካራ ግንብ መሆኑንም ነው የገለጹት።

ይህ ጀግና ትውልድ የኢትዮጵያን ክብር ጠብቆ ለሚቀጥለው የበለጸገች ሀገር ያስረክባልም ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

ጠላቶቻችን አንገቶቻቸውን ይደፋሉ ለዚህ የሚከፈል ማንኛውም መስዋዕትነት ክብር መሆኑንም አመልክተዋል።

## “በግብርናው መስክ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ኤክስፖርት ለማድረግ እየሠራን እንገኛለን። በተመሳሳይ ኢንዱስትሪ ዘርፉን ለማሳደግ እንሰራለን ብለዋል።

ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ ብልፅግና ውስጥ ትኩረት ከሚሰጣቸው አንኳር ሥራዎች አንዱ በመሆኑ ዕለቱ ዘርፉን ለመደገፍ የሚያስችል የኢንዱስትሪ ንቅናቄ ማስጀመሪያ ሆኗል፤ ንቅናቄውም በዘርፉ ውጤት እንደሚያመጣ ይታመናል ሲሉ ተናግረዋል።

በኢንዱስትሪ ዙሪያ የሚነሱ ችግሮች ሁሉም የጋራ ችግሮች እንደሆኑ በመግለፅ በዘርፉ ቀደም ተብሎ በንቅናቄ መልክ ያልተሠራበት ዋናው ምክንያት በግብርናው መስክ ቅድሚያ መሠራት የነበረባቸው ሥራዎች በመኖራቸው እንደሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

በኢንዱስትሪ ዘርፍ የምናመጣው ለውጥ እንደሌሎች ዘርፎች በቀላል የሚመጣ ባይሆንም በግብርናው መስክ ያገኘነውን ድል በኢንዱስትሪውም እንደግመዋለን ሲሉም አክለዋል።

ኢንዱስትሪ በርካታ ፈተናዎች ታልፈውና ብዙ ዓመታትን ወስዶ የሚገነባ ዘርፍ ነው። ብዙ ውጤታማ ኢንዱስትሪዎችም ለበርካታ ዓመታት ያለመታከት የተሠራባቸው ናቸውም ብለዋል።

ዘርፉ ለትውልድ የሚሸጋገር ፍሬ የምናፈራበት እንጂ በክረምት አርሰን በጥቅምት የምናጭድበት ዘርፍ አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዚህ ዘርፍ የመንግሥትም ሆነ የኢንዱስትሪ አመራሮች ገና ብዙ መማር የሚጠበቅብን መሆኑን በመገንዘብ በትግዕስት ከሠራን ውጤት ማምጣት እንችላለን ሲሉ ገልፀዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ክልሎች ለኢንዱስትሪዎች የሚሆኑ ሼዶችን ከባለሃብቶች ጋርም በጋራ በማዘጋጀት ኢንቨስትመንት ሲመጣ በቀላሉ እንዲሠራበት ማስቻል ይኖርባቸዋል። በዚህ መልክ በትብብር ከተሠራ በአጠረ ጊዜ ውስጥ ዘርፉ ሊያድግ ይችላል።

አምራቾችም በበኩላቸው የውጭ ምንዛሪ ከማምጣት ባሻገር የሀገር ውስጥ ፍጆታዎችን ለማሟላት መትጋት አለባቸው። ለዚህም የውጭ ምርቶችን መተካት በራሱ የውጭ ምንዛሪ ማምጣት እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ አስገብተው ሊሠሩ ይገባል ብለዋል።

በሀገር ውስጥ በሚገኙ ኢንዱስትሪዎች በርከት ያሉ ምርቶችን ለመተካት እየሠሩ መሆኑ የሚበረታታ መሆኑን በማንሳት፤ ከውጭ ሀገራት ብዙ ሸቀጦች እየገቡ ስለሆነ ኢንዱስትሪዎች እነዚህን ምርቶች በሀገር ውስጥ ለመተካት መሥራት ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል።

የሀገር ውስጥ ምርት እንዲበዛ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ ዜጎች በሀገራቸው የሚመረቱ ምርቶችን ሲጠቀሙና ሲደግፉ ነው፤ ኢትዮጵያውያን የሀገር ውስጥ ምርት ልንወድና ልንደግፍ ከቻልን የምናስበውን የኢንዱስትሪ ብልፅግና ልናሳካ እንችላለን ብለዋል።

በኢንዱስትሪዎች ላይ በርካታ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ አንድን ችግር ደጋግሞ በመናገር መፍትሄ ማምጣት ስለማይቻል ችግሮችን ተጋፍጦና ተቋቁሞ ማለፍ ይጠበቃልም ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ተስፋ ሰጪ ኢንዱስትሪዎች እንዳሉ በመጠቆም መንግሥት እነዚህንም ሆነ ሌሎችን ኢንዱስትሪዎች በመደገፍ ወደሚፈለገው ውጤት ለመድረስ በጋራ ይሠራል ብለዋል።

## የነዳጅ የችርቻሮ ዋጋ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የዓለም ነዳጅ ዋጋን ያገናዘበ የነዳጅ ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ለተጠቃሚው በየወቅቱ ባለመተላለፉም የተነሳ እስከ መጋቢት ወር 2014 ዓ.ም ድረስ 124 ቢሊዮን ብር እዳ ተመዝግቦ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

እስከ አሁን በህግ ወይም በአሰራር ሳይደገፍ የቆየው የነዳጅ ድጎማ በዓላማ የተገደበ አለመሆኑ፣ ተጠቃሚውን በውል ያልለየና ለብክነት የተዳረገ መሆኑን አብራርተው፣ አሰራሩን ፈትሾ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ እንደተገኘ አመልክተዋል። ለእዚህም በመንግሥት በኩል ጥልቅ ጥናት በማካሄድ አሰራሩን ለመቀየር የሚያስችል የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ አሰራር ውሳኔ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ታኅሳስ 20 ቀን 2014 ዓ.ም መጽደቁን ጠቅሰዋል።

በዚህም ውሳኔ መሰረት ቀድሞ ይሰራበት ከነበረው በተሻለ መልኩ የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማው አነስተኛ ገቢ ባላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ሊያደርስ የሚችለውን የኑሮ ጫና ለማቃለል እንደሚሰራም አስታውቀዋል። ለቀጣይ አምስት ዓመታት ለሚተገበረው የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ ሥርዓቱ እቅድ ወጥቶ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቀጣይ ሁለት ወራት የዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ በሚቀጥለው ሐምሌ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚጀመር አስታውቀዋል።

ለዚህ ትግበራ ስኬታማነት መገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ሀገራዊ እቅድ ወጥቶ ለትግበራ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። መገናኛ ብዙሃን በዚህ ረገድ ሚዛናዊ ዘገባዎችን በመስራት ኃላፊነታችሁን እንደምትወጡ አምናለሁ ሲሉም አስገንዝበዋል።

የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ አህመድ ቱሳ ከጋዜጠኞች ለቀረቡ ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት ወቅት የነዳጅ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ ሥርዓቱን መንግሥት ከዛሬ ነገ የተሻለ ነገር ይመጣል ፤ ዋጋው ባለበት ይቀጥል ፤ ትንሽ እንታገስ፤ ይቺን ወር እንለፍ እያለ እንዳቆየው ጠቅሰው፣ አሁን ነገሮች አስቸጋሪ ሆነው ሲመጡ ወደ ትግበራ ለመግባት መወሰኑን አስታውቀዋል።

አሁን ባለው አጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መተግበር ውስጥ እንደተገባም ጠቅሰው፣ ከዚህ የተሻለ ነገር ቢኖር እንዲህ አይነት ውሳኔ ውስጥ እንደማይገባም ነው ያስገነዘቡት።

በበጀት የተደገፈ፣ መንግሥት የሚከፍለው ድጎማ እንኳ ይቁም ቢባል ይህ ሰዓቱ አይደለም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣የዓለም የነዳጅ ዋጋ ጫናው በማስገደዱና ሌላ አማራጭም ባለመኖሩ እንጂ ይህ ከድጎማ የሚወጣበት ትክክለኛ ወቅት አይደለም ሲሉም አስታውቀዋል።

ይህ ህዝብ ሌላውን ችግር ተጋግዞ ተመካክሮ እንደፈታ ሁሉ ድጎማውን ለማንሳት የተቀመጠውን መፍትሄም በእዚሁ መልኩ ለማለፍ የተቀመጠ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ የተወሰነ ማስተካከያ ካልተደረገ በእስከ አሁኑ መንገድ መቀጠልና ነዳጅ መግዛት እንደማይቻል አመልክተዋል።

ነዳጅ ድርጅት ነዳጅ ለመግዛት 124 ቢሊዮን ብር ለብሄራዊ ባንክ ከፍሎ ዶላር ለማግኘት ብር ከሌለ ነዳጅ ማምጣት አይቻልም፤ ብሩ መተካት አለበት ያሉት ነዳጁን የተጠቀሙ አካላት ብሩን መተካት እንዳለባቸው ጠቅሰው፣ ለእዚህም ያለውን ፈተና ተቋቁመን የማይፈለግ መፍትሄ ትግበራ ውስጥ ገብተናል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ቁጥጥር ላይም መስራት እንደሚገባም አስታውቀዋል። ለትናንሽ ጥቅሞች ሲባል ሀገር የሚያፈርስ ህዝብን የሚጎዳ ነገር የሚፈጽሙ እንዳሉ ሁሉ፣ በዚያው ልክ በኃላፊነት የሚሰሩ አሉና እነሱን ይዞ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል ዋና ዳይሬክተሩ።

ወደ ትግበራው ለመግባት ሁለት ወራት ጊዜ እንዳለም ጠቅሰው፣በእነዚህ ሁለት ወራት የሙያተኞች ስልጠናዎች እንደሚሰጡም አስታውቀዋል። ህዝቡን የማንቃት የማስተማር የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረው የማድረግ ሥራዎች እንደሚከናወኑ፣ ሚዲያውን በመያዝ አመራሩንም ህዝቡንም ለማድረስ እንደሚሰራ ተናግረዋል።

‹‹ሥራውን የሚመራ የሚኒስትሮች ካውንስል አለ፤ ቴክኒካል ኮሚቴም ተቋቁሟል፤ ሥራውን ለመጀመር አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ተገምግሞና የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ በመንግሥት ውሳኔ እንደሚተላለፍ ጠቁመዋል።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፣ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ዛሬ እና የስብሀት ክስ የተቋረጠበት እለት፤ በጸሐፊው የህሊና ሚዛን!

ከአራት አመት በፊት የመጣው ለውጥ እንዲሳካ ማድረግ የሞት ሽረት ጉዳይ ነው በሚል ጽኑ እምነት፤ ይሄን ለውጥ በጥበብና በማስተዋል ሳንጠቀምበት ቀርተን ብናባክነው ዳግም ካለማግኘታችን በላይ አገራችንን ወደለየለት የእርስ በእርስ ግጭት ይዘፍቃትና እንደ አገር እንዳትቀጥል ሊያደርጋት ይችላል በሚል ስጋት በአልጋ ቁራኛ ፣ በደዌ ዳኛ ፤ ተይዤ ጣቶቼ ብዕር ባይዙም የእጅ ስልኬ ላይ በአውራ ጣቴ በመጻፍ እንደ ስለት ልጅ የማየው ለውጥ እንዲሳካ ሌት ተቀን እዚሁ ጋዜጣ ላይ ጽፌአለሁ። በኮቪድ ቫይረስ ተጠቅቼ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለ38 ቀናት ተኝቼ ከሞት ጋር እየታገልሁ ሳለ የሰሜን ዕዝን መጠቃት ስሰማ በቁጭትና በእልህ በመነሳሳት ከሕመሜ በላይ ሕመም ስለሆነብኝ አንድ ቀን ሳላጓድል ጽፌአለሁ። የአገራችንን ቀጣይ እጣ ፈንታ የሚበይን የወሳኝ መታጠፊያዎች /critical junctures/ ሁሉ ወሳኝ መታጠፊያ ነው ብዬ ስለማምን ያልተገባ ነጥብ ሲጥል ያመኛል። እንደ የእግር እሳት ያንገበግበኛል።

እንግዲህ በዚህ ድባብና አውድ ላይ እያለሁ ነው የእነ ስብሀትን ክስ መቋረጥ ውሳኔ ለዛውም በዕለተ ገና ስሰማ ብኹ ያለብኝና የምይዘው የምጨብጠው የጠፋብኝ። እውነት ለመናገር በህልሜም ሆነ በእውኔ ይሆናል ብዬ ያልገመትሁትና ያልጠበቅሁት ነበር። በወቅቱ ያለጊዜውና ያለምንም ገለጻ የተላለፈው ክስ የማቋረጥ ውሳኔን አንሰላስዬ ፣ አውጥቼና አውርጄ ለመረዳት ብጥርም አልተሳካልኝም። ውሳኔው እንደ የሮኬት ሳይንስ ከብዶኝ ወይም ተወሳስቦብኝ ሳይሆን ስሜቴን መግራት፣ ተጠየቃዊና አመክኗዊ መሆን ስላልቻልሁ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ መጀመሪያ በጦር ግንባር ለተሳተፉ ጋዜጠኞች በተዘጋጀ የእውቅና መድረክ በኋላ በመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት የምረቃ ስነ ስርዓት ላይ ጊዜ ወስደው የእነ ስብሀት ክስ የተቋረጠበትን ምክንያት በስፋት ቢያብራሩም፤ በስሜት ሀንጎቨር ላይ ስለነበርሁ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ የውሳኔውን ተገቢነት አምኖ ለመቀበል ተቸግሬ ነበር።

የአገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ የሚያቀርበውን የውሳኔ ሀሳብ ወይም የፍትሕ ሒደቱ ውሳኔ አልያም ብያኔ እስኪሰጥ መጠበቅ የማያስችል አጣዳፊ ሁኔታ እንኳ ቢፈጠር፤ የተጠርጣሪዎችን ክስ የማቋረጥ ውሳኔ ማብራሪያውና አንድምታው ለሕዝብ ከቀረበና ግንዛቤ ከተጨበጠ በኋላ ለዛውም የሚገለጽበት ትክክለኛ ሰዓት/timing/ በጥንቃቄ ተመርጦ መሆን ሲገባው የሕዝብንና የአገርን አቲት የወሰደ አድርጌ ስለተረዳሁት፤ የእናት አገራቸውን ጥሪ ተቀብለው የመጠ የቁርጥ ቀን ልጆቿ በአንድነት በቆሙበት ለዛውም በገና በዓል የወረደ አስደንጋጭ ዱብ እዳ ስለነበር ውሳኔውን ከግራ ከቀኝ አመዛዝኖ ለመቀበል ተቸግሬ ነበር። በነገራችን ላይ የዛን ዕለት የአገርና የሕዝብ ስትሮክ ቢኖር ኖሮ በድንጋጤ ተዝለፍልፈው ይወድቁ ነበር ። ለነገሩ ላያስችል አይሰጥም። ሆኖም ውሳኔው የፈጠረው ሀንጎቨር ዛሬ ድረስ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም።

ከዚህ ውሳኔ በኋላ አሜሪካንን ጨምሮ የምዕራባውያን ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጫና በሒደት እየቀነሰ ከመምጣቱ ባሻገር በሁለት ቀናት እስከ 74 የሚደርሱ የተዛቡ ዜናዎችን ስለአገራችን ሲያንበለብል የነበረው የምዕራባውያን ሚዲያ ሙሉ በሙሉ ላንቃው ባይዘጋም በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። ሆኖም በእነ ስብሀት ክስ መቋረጥ ከአለማቀፉ ማህበረሰብ ብዙ አውንታዊ የአጸፋ ምላሽ እጠብቅ ስለነበር ከፍ ብሎ ባነሳኋቸው ጅምር መለሳለሶች አልተደነቅሁም። አሸባሪው ሕወሓት መልሶ በአፋር ወረራ ሲፈጽም ደግሞ የእነ ስብሀት ክስ መቋረጥ እንደገና ያብሰከስከኝ ጀምሮ ነበር። ባለፈው ሐሙስ የፋና ቴሌቪዥን ዜና ላይ መክፈቻና መሪ ዜና መሆን ሲገባው በቢዝነስ ዘገባ ተወሽቆ የሰማሁት ዜና ግን የእነ ስብሀትን ክስ የማቋረጥ ውሳኔው ከአካሔዱ ባሻገር በመርህ ደረጃ ትክክል መሆኑን እንድቀበል መግፍኤ ሆኖኛል።

> **አፍሪካዊው ፋሽስት ወይም ናዚው ሕወሓት ግን የተናጠል የተኩስ አቁሙን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ፤ በሕዝባዊ ማዕበል ወደ አጎራባች የአማራና የአፋር ክልሎች ወረራውን አስፋፋ። የማይካድራው አልበቃ ብሎ በጋሊኮማ፣ በጭና፣ በአጋምሳ ፣ በንፋስ መውጫ ፣ በመርሳ፣ በውጫሌ ፣ በአንጾኪያ ገምዛ ፣ ወዘተረፈ በዘር ማጥፋት ፤ በጦር ወንጀል ፤ በሰብዓዊ ፍጡር በተፈጸመ ጥቃት የሚያስጠይቀውን ወንጀል ፈጸመ**

ባለፈው ሳምንት በዓለም ባንክና በአለማቀፉ የገንዘብ ተቋም የጋራ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ የፋይናንስ ሚኒስትሩ አሕመድ ሺዴና የብሔራዊ ባንክ ገዥው ዶ/ር ይናገር ደሴ ወደ አሜሪካ ያቀኑ ሲሆን፤ ከዚህ ጎን ለጎን በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕዛዝ በጎንዮሽ ውይይቶች ላይ የሚሳተፍ ልዑክም አብሮ ተልኮ ነበር ። በፋይናንስ ሚኒስትሩ የተመራው ይህ ልዑክ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በተቀሰቀሰው ጦርነት የተነሳ ተቀዛቅዞና ሻክሮ የነበረውን ግንኙነት ለማደስ የሚያግዙና ብዥታን የሚያጠሩ ገንቢ ውይይቶችን ማድረጉ በፋና ቴሌቪዥን ዘገባ ተመልክቷል። ልዑኩ ከአለማቀፉ የገንዘብ ተቋም(IMF)፣ ከዓለም ባንክ እና ከአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት (USAID) ጋር በመወያየት ያስመዘገበው ውጤት የእነ ስብሀት ክስ መቋረጥና መንግስት ለሰብዓዊነት ሲል የወሰዳቸው የተናጠል እርምጃዎች ተጨባጭ ውጤት ማምጣት መጀመራቸውን ያረጋግጣል።

እውነት ለመናገር በአራት ወራት ውስጥ ከገንዘብ ተቋማቱ ጋርም ሆነ ከአሜሪካ ጋር እንዲያ ሻክሮና እንዳልሆነ ሆኖ የነበረው ግንኙነት እንዲህ በአጭር ጊዜ ይሻሻላል ብሎ የጠበቀ አልነበረም። የዓለም ባንክ በሁለት አመታት ውስጥ 6 ቢሊዮን ዶላር በኮንሴሽንና በግራንት የፋይናንስ ድጋፍ ለመስጠት የተስማማ ሲሆን፤ አለማቀፉ የገንዘብ ተቋምም(IMF) አገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ለመደገፍ ቃል ገብቶ የነበር ቢሆንም በጦርነት የተነሳ የዘረጋውን እጅ አጥፎ ነበር። አሁን ግን ይህን የታጠፈ እጅ መልሶ ለመዘርጋት እና ተቋርጠው የነበሩ ተግባራትን እንደገና ለማስቀጠል መግባባት ላይ ተደርሷል። ይሄው ልዑክ ከአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ሳማንታ ፓወር ጋራ ባካሄደው ገንቢ ውይይት ተስተጓጉለው የነበሩ ፕሮጀክቶች እንደገና እንዲቀጥሉ መግባባት ደርሷል ።

ከሌሎች የአሜሪካ ተቋማት ጋር በተካሄደ ውይይትም ተፈጥሮ የነበረን ብዥታ ማጥራት መቻሉን የፋይናንስ ሚኒስትሩ ገልጸዋል። በነገራችን ላይ ይህ ታላቅ ስኬት በነጠላ ዜና ብቻ ሊታለፍ አይገባም። የመንግስት መራር ውሳኔ ያስገኘው ውጤት ከእነ ስብሀት ክስ መቋረጥና ለሰብዓዊነት ሲል መንግስት ከወሰደው የተናጠል እርምጃ ጋር አንድምታው መተንተንና መተርጎም አለበት። የመንግስት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች አገልግሎት ሚኒስትር ከፋይናንስ ሚኒስትሩ ጋር ማብራሪያ ሊሰጡበት ይገባል። ሚዲያዎቻችንም አንድምታውን በልሒቃንን ሊያስተነትኑትና ሊያብራሩት ይገባል።

ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ስመለስ፤ የፋይናንስ ሚኒስትሩን ሰሞነኛ የአሜሪካ ቆይታቸውን ለፋና የገለጹበትን ከፍ ብሎ የዘረዘርሁትን ቃለ መጠይቅ ከተመለከትሁ በኋላ ወዲያው፤ ባለፈው ጥር መጀመሪያ አካባቢ በመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት ሕንጻ ምረቃ ስነ ስርዓት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያደረጉትን ንግግር ወደ ማዳመጥ ነበር የሄድሁት። የእነ ስብሀት ክስ የተቋረጠው በሌላ በምንም ምክንያት ሳይሆን ለአገር ዘላቂ ጥቅምና አንድነት ሲባል የተወሰደ መራር እርምጃ ነው ያሉት ለካ ትክክል ነበር። በወቅቱ በውሳኔው ስሜታዊ መሆኔ ምክንያታዊ ቢሆንም ትክክል ግን አልነበርሁም። እውነትም ውሳኔው ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት የአገርን ህልውና ለማስቀጠል የተወሰደ ስትራቴጂካዊ፣ በማስተዋልና በጥበብ የተመራ ነበር። ሆኖም በወቅቱ ውሳኔው የፈጠረብኝን ስሜት እንደወረደ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ። የስብሀት ክስ የተቋረጠለት ብዕሬ እንዲህ ተንጨርጭራና ያዙኝ ልቀቁኝ ብላ ነበር። የተወሰኑ ናሙና አንቀጾችን እንደሚከተለው አቀርባቸዋለሁ። ዛሬ ከስሜት ወጥታ ስትመለከተው ግን መሳሳቷ ይገባታል። ለዚህ ነው በጸሐፊው የህሊና ሚዛን ያልሁት የመጣጥፌን ርዕስ።

ሕወሓት በተደጋጋሚ የሰላምን ደጅ ዘጋ። የተዘረጉ የሰላም እጆችን ገፋ። በመጨረሻም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ውድቅት ሌሊት ለ21 አመታት ከምሽጉ ሳይወጣ የትግራይን ሕዝብ ቀን ከሌሊት ሲጠብቀው፤ በደስታው፣ በሀዘኑና በችግሩ ተለይቶት በማያውቀው ተጋብቶ፣ ተዋልዶና አበልጅ ተናስቶ በፍቅር በኖረው ሰሜን ዕዝ ላይ ለማየት የሚዘገንን ለመስማት የሚሰቀጥጥ ክህደት በመፈጸም በውድቅት ሌሊት ትጥቅ ፈትቶ በተኛ ሰራዊት ላይ ቦንብ በመወርወርና እሩምታ በመተኮስ ጭካኔ የተሞላበት የሚዘገን ጥቃት ፈጸመ። ይፋ ያልወጡ መረጃዎች ከ6ሺህ በላይ የሰራዊቱ አባላት በገዛ ጓደኞቻቸውና ወገናቸው እንደተፈጁ ያመለክታሉ። የዕዙ የጦር መሳሪያና ስንቅ ተዘረፈ። የሰራዊቱ የጥቅምት ወር ደመወዙና በጀቱ ሳይቀር ተወሰደ። የዚህ በእነሱ አነጋገር "መብረቃዊ ጥቃት" ግብ ሰራዊቱን በማጥቃትና በመዝረፍ የሚቆም አይደለም። እንደ ግብጽ ካሉ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር በማሴርና በመቀናጀት የመንግስት ለውጥ በማምጣት ኢትዮጵያን ማፍረስ ነበር አላማው። የመጨረሻ ትልሙም በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ ታላቋን ትግራይ መመስረት ነበር። በአገሪቱ የ3ሺህ አመት ታሪክ እንደ እፉኝቱ ሕወሓት ያለ ጠላት ገጥሟት አያውቅም የሚባለው ለዚህ ነው።

ከጥቃቱ የተረፉ የሰራዊቱ አባላት በእልህና በቁጭት እንደገና ተደራጅተው ሶስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መቐሌ በመግባት የተዘረፈውን ትጥቅ በማስመለስ ወታደራዊና ፖለቲካዊ አመራሩ ተደምስሶ እጁን የሰጠው ደግሞ ለሕግ እንዲቀርብ ተደረገ። ሆኖም ከስምንት ወራት ቆይታ በኋላ በሀሰተኛ መረጃ ላይ የተመሠረተውን የምዕራባውያንን ጫና ለማስታገስ፤ ትግራዋይም የጥሞና ጊዜ እንዲያገኙ፤ ገበሬውም እንዲያርስ እና በሌሎች ሰብዓዊ ምክንያቶች ሰኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም መንግስት ከትግራይ ጦሩን ሲያስወጣ እንደ ሰሞኑ ውሳኔ አስደንጋጭና ዱብ ዕዳ ነበር። ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ኢትዮጵያዊ ውሳኔው በጥርጣሬ ቢመለከተውም ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ በኋላ አቋሙን ለዘብ አድርጎ ነበር። ሆኖም ዛሬ ድረስ ውሳኔው ስህተት ነበር ብለው የሚሞግቱ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። በአማራና በአፋር ክልሎች የተፈጸመው ግፍ፣ ውድመትና ዘረፋ የእነዚህን አካላት አተያይ የሚያጠናክር ነው።

አፍሪካዊው ፋሽስት ወይም ናዚው ሕወሓት ግን የተናጠል የተኩስ አቁሙን እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ፤ በሕዝባዊ ማዕበል ወደ አጎራባች የአማራና የአፋር ክልሎች ወረራውን አስፋፋ። የማይካድራው አልበቃ ብሎ በጋሊኮማ፣ በጭና፣ በአጋምሳ ፣ በንፋስ መውጫ ፣ በመርሳ ፣ በውጫሌ ፣ በአንጾኪያ ገምዛ ፣ ወዘተረፈ በዘር ማጥፋት ፤ በጦር ወንጀል ፤ በሰብዓዊ ፍጡር በተፈጸመ ጥቃት የሚያስጠይቀውን ወንጀል ፈጸመ። በመቶዎች በሚቆጠሩ ህጻናትና ሴቶች ላይ መነኮሳትንና አረጋውያን ጨምሮ በቡድን አስገድዶ መድፈር ፈጸመ። በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ንጹሐንን በግፍ ገደለ። ወደ 10ሺህ የሚጠጉ የጤናና የትምህርት ተቋማትን ዘረፈ። አወደመ። የመንግስትና የግል ንብረቶችን ዘረፈ። አወደመ። የወልድያ፣ የወሎና የመቅደላ ዩኒቨርሲቲዎችን አወደመ። ዘረፈ። ወደ 50 የሚጠጉ ኢንዱስትሪዎችንና ፋብሪካዎችን ዘርፎ ከጥቅም ውጭ አደረገ። ሚሊዮኖችን አፈናቀለ። እንግዲህ ሕዝብና አገር ከዚህ ትኩስና መጥፎ ትውስታ ጋር እየታገሉ፤ ሕዝቡ ከሀዘኑ ሳይጽናና፣ ከሉን ሳይቀይር ነው፤ የዚህ ሁሉ ዕልቂትና ጥፋት ስትራቴጂስት የሆነውን ስብሀት ነጋን ጨምሮ ስድስት የሕወሓት አመራሮች ለሰብዓዊነት ሲባል ከእስር የመፈታት መርዶ የተሰማው። በሀዘን ላይ ሌላ ሀዘን የፈጠረው። በበደል ላይ ሁለተኛ በደል የሆነው። የሚያሳዝነው አሸባሪው ኃይል ዛሬም ከመተናኮስ አላረፈም።

በጃዋር መሐመድና በእስክንድር ነጋ ሁለት መዝገቦች ላይ በወንጀል ተጠርጥረው በሕግ ጥላ ስር የነበሩ ሰዎች ክሳቸው ተቋርጦ እንዲፈቱ መወሰኑ ደጋፊዎቻቸውን ያስደሰተ ቢሆንም፤ በተወሰነ ደረጃ ተቃውሞ ያስነሳው በሁለት አበይት ምክንያቶች ነው። የመጀመሪያው የፍትሕ ሒደቱ ተጠናቆ ውሳኔ ከተሰጣቸው በኋላ ለአገራዊ ምክክሩም ሆነ ለብሔራዊ እርቁ ሲባል በምህረትም ሆነ በይቅርታ ቢፈቱ መልካም ነበር የሚል ሲሆን። ይህ ባለመሆኑ በሕግ የበላይነቱ ላይም ሆነ በፍትሕ ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳያሳድርና የተሳሳተ መልዕክት ወይም ትዕምርት እንዳያስተላልፍ ከሚል ቅን ስጋት የመነጨ ነው። ሁለተኛው የድምጻዊ ሀጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ በሻሸመኔ፣ በዝዋይ፣ በባሌና በሌሎች አካባቢዎች ማንነትን ኢላማ አድርገው የተፈጸሙ ጥቃቶች፣ ጥፋቶችና ውድመቶች ተመልሰው ቢከሰቱ ምን ዋስትና አለን ከሚል ስጋትና ፍርሀት የመነጨ ነው። ስጋቱ ችላ የሚባል ባይሆንም የቀውስ ቀፍቃፊው ሁለቱም ክንፎች ስለተመቱ እንዲሁም የዛን ጊዜውና የዛሬው መንግስት ሕግን የማስከበር አቅም የተለያየ ስለሆነ ስጋቱ ሙሉ በሙሉ ችላ ባይባልም ያን ያህል አሳሳቢ አይሆንም። በቀጣይ አገራዊ አንድነቱን አደጋ ላይ የሚጥሉ፤ እንደ ኤርትራ ካሉ ስትራቴጂካዊ አጋሮቻችን ጋር ያለንን ግንኙነት እንዳያሻክሩ ሰሞነኛ አይነት ውሳኔዎች ከመተላለፋቸው በፊት ግራ ቀኙን ማማከር ፤ ትርፍና ኪሳራውን ማስላት ላይ ልዩ ትኩረት ሊደረግ ይገባል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ! አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ሰውና መክሊቱ

## ‹‹ሰው በመክሊቱ ሲሰራ ይገባል››

- አቶ አቤል አዳሙ

**ሰላማዊት ውቤ**

መክሊትን ማወቅና ከመነሻ እስከ መድረሻ ሕይወት ዘመን እርስት አድርጎ መጓዝ መታደል ነው። በጉዞ የሚገጥሙትን ፈተናዎች ለማለፍ ተቀራራቢ ሙያዎችን መወጣጫ መሰላል በማድረግ ውስጥን እያዳመጡ መቆየት በራሱ ብልህነት ነው። መሆን ወደሚፈልጉትም ለመሻገር ይቀላል። ከራስ አልፎ ለብዙዎችም ፋና ለመሆን ያበቃል።

የዛሬ እንግዳችንና በአሁኑ ወቅት በፋና ብሮድካስት ኮርፖሬት የይዘት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙት አቶ አቤል አዳሙ መክሊታቸው እንዲህ ሆኖ በአውሮፓና አሜሪካ የተማሩ ጋዜጠኛ ከመሆን አልፈው ከአፍሪካ ኬንያ ብቻ ׀׀ ጊዜ ለስልጠና በመሄድ የጋዜጠኝነት ሙያን ማስተማር ችለዋል። አሜሪካና አውሮፓ ተንደላቅቀው መኖር ሲችሉ አገራቸውን በመውደዳቸው ተመልሰዋል። መመለሳቸው ለብዙ ጓደኞቻቸአልተዋጠላቸውም። ጤናቸውን ተጠራጥረው እርግጠኝነታቸውን የጠየቋቸውም ነበሩ። አገራቸው ሳትመቻቸው ቀርታ ለመመለስ ካሰቡ አበክረው እንዲጽፉላቸውና እንዲደውሉላቸውም አሳስበዋቸዋል።

ከአገራቱ ሚዲያውን በሁለት እግሩ ከሚያስቆም የሥራ ባህል ጀምሮ የግል ባህሪያቸውን ያረቁበት አስተያየትን ከገንቢ ሀሳብ በመነሳት የመስጠት ተሞክሮ አዳብረዋል። በአመራርነት በቆዩባቸውና አሁን ባሉበት ቦታ ሰውን በኔትወርክ እንዳይጎዱም አስተምሯቸዋል። ይሄ ለግለሰቡም ሆነ ለማሕበረሰቡና ለአጠቃላይ ዕድገት የሚበጅ መሆኑን አምነው እየሰሩበት ይገኛሉ። በየስርዓቱ አድርባይ እየተባለ በሚታማውና በፖለቲካ አስተምህሮ በተዋቀረው ኢቢሲ ከአራት ዓመታት በላይ ሲሰሩ አግዘዋቸዋል። አድርባይ መባሉ ከአወቃቀሩ አንፃር አለመስማማታቸውና ወገባቸውን ይዘው መሞገታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሃይማኖትና ብሔር ተቻችለው እንዲሄዱ፤ ከመንግስት ጋርም የተለያዩ መሆናቸው በተቋሙ እንዲተገበር አስችሏቸዋል። አገር ቤት ባሉ መገናኛ ብዙኃኖች ተደራሽነት ሕዝቡን የማከለ ነው ለማለት ሕዝቦች በነፃነት ፊት ለፊት መናገር የሚችሉበት ፕላት ፎርም መኖር አለበት እስከ ማለት አብቅቷቸዋል። እንግዳችን ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ ሚዲያ እንዲፈጠር ይመኛሉ። ትልቁ የአገራችን ዕድገት ጠር ድህነት ነው ብለውም ያምናሉ። የአንድ አገርና እናት ልጆችን የሚያናቁረውም ይሄው ነው ባይ ናቸው። አንዱ በሌላው መንገድ በመቆም ጠልፎ ለመጣል የሚሞክርበት የሰላም ዕጦት ምስጢርም ከዚህ የራቀ አይደለም። በመሆኑም ድህነትን ለማሸነፍና ጠንካራ ሚዲያ ለመፍጠር በፍቅርና በጋራ አገርን ለማልማት መጣር ብቸኛው አማራጫችን እንደሆነ ይመክራሉ።

ከቄስ ትምህርት ቤት ጀምረው የሰንበት ተማሪ እስኪሆኑና ለመደቆን እስኪቃረቡ ከቀለሙ ትምህርት ጎን ለጎን የቀሰሙት የአብነት ትምህርት በስነምግባር ከመቅረጽ ጀምሮ በብዙ መልኩ ለጋዜጠኝነት እንዲሰጡ አግዟቸዋል። ያለፉበትንና አሁን ያሉበትን ኃላፊነት ዕውነትን፣ ቅንነትን፣ ትዕግስትና መቻቻልን ገንዘብ አድርገው እንዲወጡና ሥራን እንዲመሩ ያደረገላቸው አበርክቶ ይልቃል። የአብሮነት መስተጋብራቸውን በማጠናከሩና የገጠሟቸውን ፈተናዎች አልፈው እንዲያሸንፉም ጥንዶቹ ትምህርቶች ዓይነተኛ መሣሪያ ሆነዋቸዋል። በመሆኑም ለዛሬ “ሰው በመክሊቱ ሊሰራ ይገባል” የሚል አቋም ያላቸውንና ስለ ሰላምና አንድነት ብቻ የሚያወራ የሚዲያ ተቋም የመፍጠር ራዕይ የሰነቁትን የአቶ አቤልን ተሞክሮ ተጋሩልን።

**ውልደትና ዕድገት**

አቶ አቤል አዳሙ በአሁኑ ወቅት በፋና ብሮድካስት ኮርፖሬት የይዘት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። የኢቢሲ የአገልግሎት ዘመናቸውን አምስት ዓመታት ለመድፈን የሶስት ወራት ዕድሜ ሲቀረው ነው ወደ ፋና ብሮድካስት የመጡት። እንግዳችን ከሌሎቹ የኢቢሲ ሥራ አመራሮች በሁለት ነገር ይለያሉ። አንዱ በኢቢሲ ታሪክ ከአራት ዓመታት በላይ በአመራርነት በመቆየት ቀዳሚ መሆናቸው ሲሆን፤ ሌላው ሳይሻሩ ወይም ሳይባረሩ በደብዳቤ ወደ ፋና ብሮድካስት ተጠይቀው መምጣታቸው ነው፡፡ ትዳር መሥርተው ሦስት ሴት ልጆችን አፍርተዋል። የመጀመሪያ ልጃቸው ׀׀፤ ሁለተኛዋ ድግሞ ሰባት ሲሆናት ትንሿ አራት ዓመቷን አስቆጥራለች። ትውልዳቸው የአባይ ወንዝ መነሻ አካባቢ በምትገኘው የደቡብ ሜጫ ዋና ከተማ መራዊ ነው። በውል የማያስታውሷቸውን አባታቸውን በህፃንነታቸው በሞት በማጣታቸው ዕድገታቸው ባህር ዳር ከተማ ይኖሩ የነበሩት አጎታቸው ጋር ለመሆን ተገድዷል። ፊደል መቁጠር የጀመሩትም በባህር ዳር ከተማ አጎታቸው ቤት ተቀምጠው ነው፡፡ ሟቹ አባታቸውንና የእህቶቻቸውን ባሎች ጨምሮ ቤተሰቦቻቸው ጠለቅ ብለው የክህነት ትምህርት የቀሰሙ ቀሳውስት ናቸው። ያኔ ትምህርቱ በፈረቃ መሆኑ ግማሽ ቀን የቀለሙን ግማሽ ቀን ደግሞ ይሄን የቤተሰባቸውን የክህነት ትምህርት ለመማር የሚያስችል ሰፊ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ከመምራትና ካህን ሲቀር ከመስበክ አልፈው ባይደቁኑም እሳቸውም አዳራቸውን አብነት ትምህርት ቤቶች በማድረግ ትምህርቱን ከቀለም ትምህርት ጎን ለጎን ሲቀስሙት ነው የኖሩት።

**ፈተና**

እንግዳችን አቶ አቤል በሕይወት መፈተን የጀመሩትም ከዚሁ ከልጅነታቸው ጀምሮ ገና በአጎታቸው ቤት ሳሉ ነው። ድህነት፣ ማጣት ምን እንደሆነ በሙሉ ቀለም በራሳቸው ሕይወት ውስጥ አይተውታል። የሚቀይሩት ጫማና የሚበሉት አጥተው የተጨነቁበትና እስከ መሸከም የዘለቀ ሥራ ለመሥራት የተመኙበትና ምግብ ወዳለበት ሥፍራ ዓይናቸው ያማተረበት ቀንም ገጥሟቸዋል። ይሄ ሕይወታቸውን በዕቅድ መምራት፣ ሲያገኙ አለማባከን ሲያጡም አለመቆዘምን አስተምሯቸው፤ አንድ ቀን ሰው እሆንና ከችግር እላቀቃለሁ የሚል ተስፋም እንዲኖራቸው አድርጓቸው አልፏል። እንዳወጉን የቀለምና የአብነት ትምህርቱን አጣምረው መሄዳቸው ለአጎታቸው ታዛዥ እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። ጠዋት ሥራ ሲሄዱ ያዘዟቸውን ማታ ሲመለሱ ሰርተው ሲቆይዋቸው ኖረዋል። ለዚህ ማበረታቻ ይሆናቸው ዘንድ አጎታቸው ልብስና ጫማ ሲገዙላቸው ቆይተዋል። ምንጩ ከዕውነታ ጋር የተያያዘ ቢመስልም ግትር የሚያስመስል ባህርያቸውንም (ፍሌክሴብል) እንዲያደርጉም ሸንቆጥ ያደርጓቸው ነበር። በመካከሉ ዛሬ ሲያስቡት እጅግ ቀላል ቢሆንም አሁን በሕይወት ከሌሉት ከአጎታቸው ባለቤት ጋር ተጋጩ፡፡ ትዳርህን አልበጠብጥም ብለው ከቤት የወጡትም በዚሁ ባህርያቸው ይመስላቸዋል። ወጥተው ማደሪያ አጥተው ተንከራትተዋል። ከቤት ወጥቶ ከውጭ የማደሩም ሆነ ማደሪያ ቦታዎችን የማወቅ ልምዱ ስላልነበራቸው በእጅጉ ተቸግረዋል። ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ ዙሪያው ተቆልፏል። የቤተክርስቲያንቱ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋይና ተማሪ በመሆናቸው ጥበቃዎች ቢያውቋቸውም ከአጎቴ ስለተጣላሁና ማደሪያ ስላጣሁ በሩን ክፍቱና አስገቡኝ ለማለት ይሉንታና አፍረት ያዛቸው። በሁለቱም ወገን የጀመሩት ትምህርታቸው ማደሪያ ባለማግኘታቸው ሊቋረጥ መሆኑም አብዝቶ አስግቷቸዋልና አማራጫቸው የቤተክርስቲያኑን አጥር ተደግፈው መተኛት ቢሆንም እንቅልፍ አልመጣ አላቸውም።

ሲጨንቃቸውና ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን ይወድዱትና ይግባቡት ለነበረ አንድ ፀጋዬ ወርቁ ለተሰኘ መጽሐፍ ነጋዴ ወዳጃቸው ደወሉለት። ምንም ሳይኖረው ሰው የሚረዳ መሆኑን ያውቁ ነበርና ወደ ቤቱም ሄደው ክፈትልኝ ሲሉት ሰውዬው ደነገጠ። እንዳሰቡት ትምህርታቸው ፈፅሞ እንደማይቋረጥ ካገኙ እንደሚበሉ ካጡ ጦማቸውን እንደሚያድሩ በመግለፅ አበረታታቸው። መጽሐፍ ነጋዴው እያሳደራቸውና ያገኘውን ሳንቲም እያካፈላቸው እንዲሁም የሚያውቋቸው ሰዎች ጠርተዋቸው ቡና፣ ሻሂ እየላቸውና ምሳ እየጋበዟቸው



ፎቶ ፡- ናኦል አየለ

ኑሯቸውን ሲገፉ ቆዩ። የአብነቱንም ሆነ የቀለሙ ትምህርታቸው እንዴትና የት ሆነው መማር እንደሚችሉ ግራ በገባቸው ወቅት ወላጆቻቸውን የሚያውቁና አሁን በሕይወት የሌሉት መላከ ገነት መምሬ ኃይለማርያም አዳሪ የቤተክርስቲያን ትምህርት ቤት ያስገቧቸው መሆኑ የትምህርት ፍላጎታቸውን ዳር ከማድረስ ባሻገር ማደሪያ በማጣት ሊደርስባቸው የሚችለውን ከባድ ፈተና አቅልሎላቸዋል።

**የአብነትና የዘመናዊ ትምህርት**

አቶ አቤል የአብነቱንና የቀለሙን ትምህርት ጎን ለጎን ማስኬዳቸውን ቀጥለዋል። በቀለሙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በአብነቱም ሰንበት ትምህርት ቤትን በሊቀ መንበርነት እስከ መምራትና ካህን ሳይኖር አውደ መንበር ላይ ተሰይመው መዘመርና

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ



ምእምናን እስከ መስበክ ዘለቁ። በዚህ መካከል ያገኝዋት የትምህርት ቤት ጓደኛቸው ዛራ በዕምነት ባትመስላቸውም በውስጣቸው ትልቅ ቦታ ነበራት። የእሷም የእሳቸውም በዓላት ሲኖሩ በጋራ እየበሉና እየጠጡ የሚያሳልፉት ዛሬም ድረስ አይረሳቸው። ቤተክርስቲያን ሲሰብኩ ውለው በልጅነቷ ትዳር መስርታ ልጆች ለማፍራት ከበቃቸው ዛራ ባለቤትና ቤተሰብ ጋር ጎራ ካላሉ ምነው ዘገየህና ቀረህ ተብሎ ቤተክርስቲያን ድረስ ሰው ይላክባቸዋል። በዚህ ባለፉበት ዘመን በተለይ ክርስትና እና እስልምና ሃይማኖት በእቁብ፣ በዕድርና በማንኛውም ማህበራዊ ሕይወት ተደጋግፈው ይሄዱ የነበረ መሆኑን ፈፅመው አይዘነጉትም። እንደውም ባደጉበትና በተማሩበት ባህር ዳር ከተማ ውስጥ በህብታቸውና በትልቅ ሰውነታቸው እጅግ የተከበሩ አንድ ታላቅ የእስልምና ሃይማኖት አባት ሲሞቱ ሙስሊሞች በአንድ በኩል ዱአ ሲያደርጉ ካህናት በበኩላቸው ፍትሃት ያደርጉበት የነበረው የልጅነት ትውስታቸው ከአእምሯቸው ተፍቆ አልጠፋም። የትምህርት ቤት ቆይታቸው ቀይ መስቀል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡበትም ነበርና እዚህ የሚሰሩ ሰዎች የሚሰጧቸውን ብር ስለ ማይጠጡና ምንም ዓይነት ሱስ ስለሌለባቸው ለክፉ ቀን እያሉም ቋጠሩ። ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የትምህርት ስርዓት አካሄድ ብዙ ጊዜ ተማሪው በፈለገው ሳይሆን ትምህርቱ በመራው እንደመሄዱ ዓላማቸው ቋንቋ ማጥናት ባይሆንምና ብዙ የሚያውቋቸው ሰዎች ኢንጂነር ወይም ዶክተር ይሆናሉ ብለው ሲጠብቋቸው እንግዳችን የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው በቋጠሯት አራት ሺህ ብር ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቋንቋ ዲፕሎማ ለመያዝ በቁ።

**የሥራ ዓለምና ራስን በትምህርት እያበለጸጉ የመሄድ ጥረት**

እንግዳችን ጋዋን ከመልበሳቸው በፊት ለመጀመሪያ ጊዜ አማራ መገናኛ ብዙሃን ኤጀንሲ ባወጣው ክፍት የሥራ ቦታ ተወዳድረው ወደሚወዱትና መሆን ወደሚፈልጉት የጋዜጠኝነት ሙያ ገቡ። ‹የምሆነውን ስላገኘሁ የያዝኩትን መውደድ አለብኝ› አሉና በዚሁ ዙሪያ ማሸነፍና ወደፊት መግፋት የሚያስችላቸውን ጥረት ቀጠሉ፡፡ ትግላቸው ቀላል አልነበረም፡፡ ደሞዛቸው 347 ብር ነበር። ከዚህ በየወሩ ከሚያገኙት 200 ብሯን ማስቀመጡን ተያያዙት። በሰሩበት አንድ ዓመት ውስጥ 2ሺህ 400 ብር ሲሆንላቸው በመደበኛው የትምህርት መርሐ ግብር የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን ለመማር ተወዳድረው አለፉና ያጠራቀሙትን ትራንስፖርት አድርገው ከባህር ዳር ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጓዙ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በቋንቋዎችና ስነጽሑፍ በማስተማር ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በመያዝ በጋዜጠኝነት ሙያ ሊያሰራቸው የሚችለውን ትምህርት ዝግጅት አሻሻሉ፡፡

ያሻሻሉበት መንገድ አልጋ በአልጋ አልነበረም። በልጅነታቸው የጀመራቸው ችግር እዚህ ላይም የሚያደርጉት ጫማ፤ የሚበሉት እንጀራ እስከ ማሳጣት በብርቱ ፈትኗቸዋል። ለዕውቀት ሳይሆን ፈተና ለማለፍ ብለው በሽምደዳ የሚሰቅሉ ተማሪዎች መበራከት ሌላው ፈታኛቸው ነበር። ለዕውቀት እንዲሰሩ መምከር ተጨማሪ ሥራ ሆኖባቸዋል። አሁን አሜሪካ ካለው ከእሳቸው ዓይነት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ከነበረው ጓደኛቸው ጋር በዩኒቨርሲቲው ካፌ እየተመገቡና ሰው የሚሰጣቸውን ለፈተና ሰሞን ለ15 እና ለ30 ሳንቲሙ ሻሂና ቡና መጠጫ እያኖሩ ነው የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራማቸውን የተከታተሉት። ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ራሳቸውን ባደጉበት በመንፈሳዊ ሕይወት ማነፃቸውንም አልተውም። ቢሆንም ከትምህርት ጊዚያቸው ጋር የሚሄድ ሰባኪና ቤተክርስቲያን ያማርጡ ነበር። በአብዛኛው ከጊዚያቸው ጋር የሚሄድላቸው 11 ተኩል ተጀምሮ 12 ተኩል የሚያልቀው የስድስት ኪሎው ምስካየ ኅዙናን መድሃኒ ዓለም ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ትምህርትን መከታተል ይቀናቸዋል። ከዚህ በጎነትን፣ ትዕግስትን፣ ያለውን ከሌላው ጋር ተካፍሎ እስከ መብላትና እስከ መጠጣት የሚያደርስ የማህበራዊ ሕይወት መስተጋብርን መካን ችለዋል። ወደ ካምፓስ ቆይታቸው ስንመለስ ራት ከበሉና ወረፋ ይዘው ቡና ከጠጡ በኋላ ደብተራቸውን ይዘው ለማጥናትና ለማንበብ ኬኔዲ ቤተ መጻሕፍት በመግባት እስከሚዘጋበት፣ ምሽቱ አራት ሰዓት ያጠናሉ። ለ”ግሬድ” ብለው የሚያጠኑ ግን አልነበሩም። ጋዜጠኛ ለመሆን ስለሚያስቡ የሚያነቡት በአብዛኛው የጥቁር አፍሪካን፤ ከአክሱማዊ ዘመን አንስቶ እስከ ዘመናዊ ስነጽሑፍ የነበረውን የኢትዮጵያ ታሪክ ነበር። ሽምዳጆችን ማስረዳቱና አብሮ ማጥናቱ የበለጠ እያጠነከራቸውና መንፈሳዊው ትምህርት ከጥረታቸውና ከጠንቃቃነታቸው ጋር ተደማምሮ አጽንቷቸው ፈተናውን በማለፍ የመጀመርያ ዲግሪ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ነጥብ በማጠናቀቅ ወደ አማራ ክልል መገናኛ ብዙሃን ተመልሰው በጋዜጠኝነት ሙያቸው ቀጥለው ለአንድ ዓመት ሰርተዋል።

ጋዜጠኝነት ያዩትን ፊት ለፊት መናገር፣ መረጃ ፈልጎ ማውራት ነው ብለው ያምናሉ። ሆኖም ይሄ በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ ያለ ዕምነትና አስተሳሰባቸው በብዙዎች ሰዎች እይታ ነውጠኛ አስመሰላቸው። እንደውም ወዳጆቼ ያሏቸው ጋዜጠኝነት እንደዚህ አይደለም፤ ለአንተ አይሆንም፣ ለምን ሙያ አትቀይርም እያሉ መከሯቸው። አዳሪ ት/ቤት ሲማሩም ሆነ ከልጅነታቸው ጀምሮ የነበራቸው ፍላጎት የተለያዩ ስነጽሑፎችን ማንበብ፣ መፃፍ፣ ቲያትር መድረስ፣ ጋዜጠኛ መሆን፣ ሪፖርት ማድረግ ነበር። ሆኖም በሁለት ዓመታት የጋዜጠኝነት የአገልግሎት ጊዜያቸው በሙያው ብዙም የተካኑና ተሰጥኦ ያላቸው ስላልመሰላቸው፤ ይሄንኑም አንዳንድ ወዳጆቻቸው ስላረጋገጡላቸው ከጋዜጠኝነት ሙያው ሌላ ለእሳቸው ባህርይ የሚስማማ የሙያ አማራጭ መፈለግ እንዳለባቸው አሰቡ። አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ማስታወቂያ ሲያወጣ በዩኒቨርሲቲው በመምህርነት ተቀጠሩ። አርባ ምንጭ አንድ ዓመት ካስተማሩ በኋላ ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ጋር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን ቀጠሉ። ሆኖም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በመለወጡና አካሄዱን ባለማወቁ ደመወዛቸው ተቋረጠ። እንግዳችን አርባ ምንጭን ቢወዱትም ይሄው ምክንያት ሆኗቸው ወደ ዩኒቨርሲቲው ሄደው ለምን ደመወዜ ተቋረጠ ብለው ሳይጠይቁ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን እንደያዙ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ትምህርት ክፍል በመምህርነት ተቀጥረው ማገልገል ጀመሩ ።

እዚህ እያስተማሩ የትምህርት ዝግጅታቸውን በየጊዜው ከማሳደግ አልቦዘኑም። በተለያየ አቅጣጫ ጥረቶችን ያደርጉ ነበር። ‹‹ኢራስሙስ ሞንድስ›› የተሰኘ የአውሮፓ ሕብረት ነፃ የትምህርት ዕድል ተወዳደሩና አሸነፉ። ወደ አውሮፓ በመዝለቅም ‹‹ላይፐዚግ›› የተሰኘ ከተማ የጋዜጠኝነት ትምህርት በመማር ሌላ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ሰሩ። ትምህርቱ ይቀሰም የነበረው ከተለያየ ዩኒቨርሲቲ መሆኑ የአውሮፓን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ቦታዎችን ለማወቅ ዕድል ሰጥቷቸዋል። የመጀመሪያውን ሴሚስተር በሆላንድ ዋና ከተማ አምስተርዳም ተማሩ። ጀርመን ሐምቡርግ ዩኒቨርሲቲ አንድ ዓመት፤ በድምሩ ሁለት ዓመት በመቆየት ትምህርታቸውን ጨረሱ። በትምህርቱ ለሰው ልጆች ስለሰብዓዊነት ማውራት፣ ዕውነትን መናገር፣ ያልታወቁ ነገሮችን ማሳወቅና ብዙ ቁም ነገሮችን በመቅሰማቸው ጋዜጠኛ የመሆን ፍላጎታቸው የበለጠ ጨመረ።

በቪኦኤ ውስጥ ሆርን ኦፍ አፍሪካ (የአፍሪካ ቀንድ) የተሰኘ ፕሮግራም በመጀመሩም ፈጥነው በአፓራንትሺፕ መልክ ለነፃ የበጎ ፈቃድ ሥራ አመለከቱ። የሥራ ልምዳቸውንና የትምህርት ዝግጅታቸውን ዓይተው ስለፈቀዱላቸው ወደ አሜሪካ አቀኑ። አልድዌ በተሰኘ ሥፍራም ሰሩ።

**ከአሜሪካ ወደ አገር ቤትና የኢቢሲ ቆይታ**

እንግዳችን እዚህ ጣቢያ ላይ በቋሚነት ተቀጥረውም ሆነ በሌላ ዓለም አቀፍ ሚዲያ የሚያሰራ ልምድና ዕድል ቢኖራቸውም በብዙ ምክንያቶች ወደ አገራቸው ተመልሰው መጡ። አንዱ አገራቸውን መውደዳቸው ሲሆን ሌላው ውጭ አገር ሆነው ወደ ኢትዮጵያ ሲያስቡ እዚህ አገር የሚሰሩት ልዩነት መፍጠር የሚችሉበት አወንታዊ አመለካከትና ዕውቀት መኖር ነበር። ወደ አገር ቤት እከሌ የሰራው የሚባልለት ሥራ ሰንቀው በመመለስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከነበረው የማስተማር ሥራቸው በተጓዳኝ ባህር ማዶ የቀሰሙትን ዕውቀት መሰረት አድርገው በሊንክ የሚሰራ የዩኒቨርሲቲውን ፕሮፋይል የመሥራት ጥረት ሲያደርጉ ቆዩ። በወቅቱ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት የነበሩት ፕሮፌሰር አድማሱ ፀጋዬ እሳቸው የሚሰሩበትን የጋዜጠኝነት ትምህርት ክፍል ሊጎበኙ ሲመጡ ለምን ሬዲዮ ጣቢያ አይኖራችሁም? ሲሉ ይጠይቃሉ። እንግዳችን ከዚህ በፊት ሞክረው ያውቃሉና መልስ ሳይሰጡ ዝም ይላሉ። ፕሬዚዳንቱ በፊናቸው ለሥራ ያላቸውን ፍቅርና ችሎታም ያውቃሉና አጥብቀው ይይዟቸዋል። ብዙ ሰው እንደሞከረና እንዳልተሳካ እሳቸው እገዛቸውን የሚያደርጉ ከሆነ ግን ያለ ሌላ ምንም ሰው በራሳቸው እንደሚያሳኩት ይገልፁላቸዋል። በፕሬዚዳንቱ ከፍተኛ ድጋፍ በመታገዝ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ሬዲዮ 99 ነጥብ አራትን ለማቋቋም በቁ። ይህን ተማሪዎቼ ከወዲሁ ይለማመዱበታል ያሉትን ሬዲዮ ለማቋቋም ከፕሮፖዛል ዝግጅት አንስቶ በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፈዋል። ብዙ ፈተናዎች ገጥሟቸዋል። አንዱ አብረዋቸው ጋዜጠኝነት የሚያስተምሩ መምህራን እንኳን የማህበረሰብ ሬዲዮ መቋቋሙን አለመደገፋቸው ነበር። ሆኖም መልካም ተግባራቸው ኢቢሲን የመቀየር ፍላጎት በኢቢሲ የቦርድ አባላት ላይ እንዲያድርባቸው አደረገ፡፡ ብዙዎቹ የአሰራሩን ዘዴ እንዲጠይቋቸው በርም ከፈተ። ለዶክተር ነገሬ ሌንጮ ፎርማት በመቀየር እንደሚያግዙ ምላሽ ሰጧቸው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ወደ ኢቢሲ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆነው መጡ።

የለውጥ ሀዋርያ የሆኑት አቶ አቤል ወደ ስፖርቱንም፣ መዝናኛውንም፣ ዜናውንና ማንኛውንም ፕሮግራም በአንድ ብቸኛ ቻናል ሲያከናውን ለነበረው ለትልቁ የአገር ሀብት ኢቢሲ ቀላል ብስራት አልነበረም። በመሆኑም በወቅቱ በነበሩት የኢቢሲ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሞቅ ያለ አቀባበል ተደርጎላቸውና የዜና ቻናሉ ፎርማት ዋና መሪ ሆነው ወደ ሥራ ገቡ። ሦስት ያህል ቻናሎችንም ቀየሩ። በየዘመኑ ለሚለወጠው ስርዓት በማገልገሉ አድርባይ የሚል ስያሜ የተሰጠውን ኢቢሲ አሰራርም በመለወጡ ረገድ ዓይነተኛ ሚና ተጫውተዋል። ጡሩንባ ነፊ እስከ መባል በመድረስ በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የሚብጠለጠልበትን አመለካከት ይቃወማሉ። ኢቢሲ ነፃና ገለልተኛ ሆኖ በመሥራቱ በሚታማበት ጉዳይ በዓለም ላይ ነፃ የሆነ ሚዲያ የለም ሲሉ ጥብቅና ይቆሙለታል። የሚመራው አመራርም ፓርላማ በተመረጠ ፖለቲከኛ ተሾሞ ነፃ ይሆናል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት መሆኑንም ዋቢ ያደርጋሉ። ሆኖም በእሳቸው ጊዜ በተቻለ መጠን ኤዲቶሪያል ስርዓቱን ነፃ ለማድረግ መሞከሩን አልሸሸጉም። ሕዝቡ በተለይም አንዳንድ ሰዎች ስለ ኢቢሲ ያላቸው አመለካከት መዛባቱ ያሳዘናቸዋል። ግን ደግሞ ካለማወቁ የመነጨ መሆኑን ይረዳሉ። ከዚሁ ካለማወቅ አኳያ ለበዓል አየር ሽፋን ድጋፍ እንዲያደርጉ የተጠየቁ ትልቅ ሰው (ባለሀብት) ‹‹ሂድ! ምድረ ጡሩንባ ነፊ መንግስት አይሰጣችሁም እንዴ” ያሉበትን አግባብ ያወሳሉ። ኢቢሲን ከዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ለማዳን ኤዲቶሪያል በሚሰበሰቡበት ጊዜ ሁለት ነገሮች ይጠነቀቃሉ።

የመጀመሪያው፣ ሁሉም ሃይማኖቶች ከሌላው የማይበላለጡ እኩል በመሆናቸው አንደኛውን ሃይማኖት ከሌላው ሃይማኖት የሚያጋጭ፣ የሚያበላልጥና የሚያሳንስ ዘገባ ፍፁም እንዳይስተናገድ ማድረግ ነው። ሁለተኛው፣ ብሔርን ከብሔር የሚያጋጭ ወይም የሚለይ ዘገባ አለማስተናገድ ነበር። ጋዜጠኝነት ሰው በሰውነቱ እኩል የሚስተናገድበትን ዕድል መስጠት አለበት። በኢቢሲ በሚስተናገዱ ዘገባዎች እንዲህ ዓይነቱ ጥንቃቄ እንዲደረግበት ሰርክ ያስገነዝባሉ። ምስሎች ላይም ሆነ ጽሑፎች ላይ ያላሰለሰ ቁጥጥርም ይደረጋል። በተለይ ምስሎች ተደጋግመው እንዳይሄዱና ያልሆነ ትርጉም ተሰጥቷቸው ችግር እንዳይፈጥሩ ይፈለጋል። እንደሳቸው በኢቢሲ ከዚህ አምልጦ ለአየር የበቃ የለም ለማለት ይቸገራሉ። በአንድ ወቅት በቡራዩ በነበረው ግጭት የሆነውን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ። ተግባሩ የአንድ ሰው ድምፅ ወስዶ ለቢሊዮን በሚያደርሰው ኢቢሲ ላይ ብዙ ችግር እንዳስከተለበት ያስታውሳሉ። ባይጎሉም የተሰጣቸውን አቅጣጫ ቀይረው በሚሰሩ ጋዜጠኞች ሽወዳ የሚፈጠሩ ስህተቶች ነበሩ። በእሳቸው ዘመን አንዳንድ በመደበኛው ፕሮግራም ስሜታዊ ሆነው ሲናገሩ ይቆረጣል። ተቆርጦ ይጣልብኛል ያለ ታዲያ ኢቢሲ ቀጥታ ስርጭት ውይይት ላይ መጥቶ ተሳድቦ የሚሄድበት ሁኔታ ሁሉ ገጥሞ ያውቃል።

ኢቢሲ ሶማሌ ክልል ከኦሮሚያ ክልል ጋር ሲጣላ የሶማሌ ክልል ይደውልና “ኦሮሞ ሶማሌን እየገደለ ነው ብላችሁ የማትዘግቡት ለምንድ ነው?” ይላል። ኦሮሚያ ክልል ይደውልና “ሶማሌ ኦሮሞን እየገደለና እያፈናቀለ ነው ብላችሁ ዘግቡልን” ይላል። ሆኖም ተቋሙ ከሁለቱም ቦታ ሰዎች መፈናቀላቸውንና የሞት መኖሩን አስቸኳይ እርዳታ አስፈላጊ መሆኑን እንጂ እከሌ እከሌን ገድሎታል ብሎ አይዘግብም። እንደ እንግዳችን ታዲያ በኋላ ቢመሰገንበትም በኢህአዴግ ስርዓት ይሄን ባለማድረጉ ኢቢሲ ሲወቀስ የነበረበት ጊዜ ቀላል አልነበረም። ኢቢሲ የሰው ልጅ በመልካም ግንኙነት አብሮ እንዲኖር፣ ሰላም እንዲሰፍንና ልማት እንዲመጣ የሚሰራ ነው እንጂ ግጭት የሚፈጥር አይደለም። ሃይማኖት ይኖራል፤ ሕዝቦችም ይኖራሉ፤ አገርም እንዲሁ ህያው ነች። ፖለቲከኛም ያልፋል። በመሆኑም እማያልፍን ነገር መሥራት ይሻላል የሚል አቋም አላቸው። እንደ እሳቸው ጋዜጠኝነት ማለት ሰብዓዊነት ነው። በዚህ መልኩ ሥራውን እንዲያከናውን መንግስት ከውጭ የሚገቡ ግብዓቶችን ከቀረጥ ነፃ በማድረግ ችግሮቹን መፍታት አለበት ብለው ያምናሉ። ፋናም በዚሁ መልኩ እየሰራና እየታገለ ይገኛል። ፋና ብሮድካስት ኮርፖሬት የጋዜጠኝነት ሙያ ያላቸውና ሥራቸውን አድምተው የሚሰሩ ባለሙያዎች ያሉበት የሚዲያ ተቋም ነው። እሳቸው ፋና ጠንካራ ሚዲያ እንዲሆንና አሁን አገራችን ካለችበት ያለመግባባት ችግር ለመላቀቅ በሰላምና አንድነት የሚሰብክ ሚዲያ ብቻ እንዲኖር የማድረግ ራእያቸውን የሚያሳካ ሚዲያ እንዲኖር ከማድረግ አልፎ ፋናንም እዚህ ደረጃ ለማድረስ እየሰሩ ይገኛል።

# ባህልና ቱሪዝም

## ሹዋሊድ- በሃረሪ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እኛ ኢትዮጵያውያን “ውብ ድብልቅ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቅርስ፣ ታሪክ እንዲሁም ማንነት ያለን ህዝቦች ነን” ስንል እንዲያው ዝም ብለን አይደለም። ይልቁኑ በዓይን የሚታዩ፣ በእጅ የሚዳሰሱ፣ ያለምንም ችግር በህሊና ፍርድ የሚሰጣቸውና ምስክር የማያሻቸው በመሆናቸው ጭምር እንጂ። ለዚህ ነው የኛ ያልሆነውን ሁሉ አግበስብሰንና ህሊናችንን አውረን ለመታበይ የማንፈልገው። በዓለም መድረክ ላይ ረብጣ ገንዘቦችን አውጥተን የማስተዋወቅ እድሉን ባናገኝ እንኳን ዓለም ደጃፋችን ድረስ መጥቶ እውነታውን ቆፍሮ እንዲያገኝ እሴቶቻችን በራሳቸው አፍ አውጥተው የሚናገሩ ናቸው።

ከእነዚህ ውብ እሴቶች መካከል ለዛሬው ወደ ምስራቅ ተጉዘን በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የረመዳን ፆም እንዳበቃ የሚጀመረውን የሸዋል ኢድ እናስተዋውቃችኋለን። በተለይ በሃረሪ ክልል ይህ ሃይማኖታዊ ስርዓት ሌሎች የማህበረሰቡን እሴቶች ጨምሮ ባህላዊ ስነ ስርዓትን አካትቶ በደማቅ ሁኔታ ይከበራል። ይህን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ስነ ስርዓት በተመለከተ የሃረሪ ክልላዊ መንግስት ባህል ቅርስ ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ተወለዳ አብደሽ “የሃረሪ ብሔረሰብ የማይዳሰሱ ቅርሶች ክንዋኔዎችና ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ስነ ስርዓቶች” ጥናትን መነሻ አድርገው እንደሚከተለው አብራርተውልናል።

**ሹዋልኢድ**

የሹዋሊድ ክብረ በዓል በእስልምና ሃይማኖት ያሉ አጽዋማትን (የጾም ወቅትን) ማንኛውም ለአቅም አዳምና ሄዋን የደረሰ የእምነቱ ተከታይ መጾም ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው። ከእነዚህም መካከል ዋናው የጾም ወቅት የረመዳን ወር ጾም ነው። የሹዋል ፆም በእስልምና እምነት የረመዳን ወር ጾም እንደተጠናቀቀ የሚጀመር ነው። በሹዋል ወር የመጀመሪያው ቀን የዒድ አልፈጥር በዓል ይከበራል። ከሹዋል ሁለተኛው ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ስድስት ቀናት ደግሞ የሹዋል ጾም ይጾማል። ይህ ጾም በሹዋል ወር የሚጾም በመሆኑ ስያሜውን ከወሩ አግኝቷል። የሹዋል ጾምን ነብዩ መሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) በሕይወት ዘመናቸው ሲጾሙት የነበረ ጾምና በሹዋል ወር ስድስት ቀናትን የጾመ ዓመቱን በሙሉ እንደጾመ ይቆጠራል የሚል አስተምህሮት ያላቸው በመሆኑ የሹዋል ጾም በዚሁ መነሻነት በሐረሪዎች ዘንድ ከጥንት ጀምሮ መጾም እንደተጀመረ ይነገራል። የሹዋል ጾም በፍላጎት የሚጾም የሱና ጾም ነው። ሱና ስንል የነብዩ መሐመድ ወይም የረሱልን አስተምህሮ የተከተለ፣ አጅር ወይም ምንዳ የሚገኝበት፣ በረመዳን ጾም በምክንያት የተፈታን ጾም ለማሟላትና ሃይማኖታዊ አስተምህሮትን መተግበርን ሁሉ የሚያካትት ነው።

በሃይማኖቱ የሹዋልን ጾም በተከታታይም ሆነ ነጣጥሎ መጾም ይቻላል። ሁለቱም የአጿጿም ስልት ደረጃቸው እኩል ነው። ይሁንና ከዒድ አልፈጥር በኋላ ያሉትን ስድስት ቀናት በተከታታይ መጾም ግን የበለጠ ዋጋ አለው። እንደሚታወቀው ሴቶች በተፈጥሮ አስገዳጅነት ምክንያት በረመዳን የጾም ወቅት የወር አበባ በሚያዩባቸው ቀናት ጾሙን ለማቋረጥ መገደዳቸው አይቀሬ ነው። ይህን ያቋረጡትን ወይም ያጓደሉትን የጾም ቀናትም በሹዋል ጾም ማካካስ ይጠበቅባቸዋል። 138 ምንም እንኳ በሃይማኖቱ በወሩ በማንኛውም ጊዜ ማካካስ እንደሚቻል ቢጠቀስም በሐረሪዎች ዘንድ ከጥንት ጀምሮ በተከታታይ መጾሙ እንደ ባህል ተይዞ የመጣ ነው። ለዚህም መነሻቸው የሴቶችን ጫና ከመቀነስ አንፃር፣ ሴቶች ለብቻቸው ከሚጾሙ ሁሉም የቤተሰቡ አባላት በጋራ መጾሙ አብሮነትን፣ መተሳሰብንና መደጋገፍን ያጎለብታል በሚል አስተሳሰብ ነው። ከዚያም ባለፈ በመጾማችን ከአላህ ወይም ፈጣሪ የምናገኘው አጅሪ ወይንም ምንዳ ከፍተኛ ነው በማለት ያምናሉ። በዚህም መሠረት ጾሙን ከስራ ባህላቸው ጋር እንዲስማማ አድርገው ባህልና ወጋቸውን በጠበቀ መልኩ ስድስቱን ቀናት በተከታታይ በመጾም የሹዋሊድን በዓል ያለምንም የጾታ፣ ዕድሜና ማኀበራዊ ደረጃ ገደብ ሁሉንም ባሳተፈ መልኩ በደመቀ ሁኔታና ባህላዊ እሴቶቻቸውን በሚያንጸባርቅ መልኩ እየተከበረ ይገኛል።

ይህም ባህላዊ ቅርሱን የብሔረሰቡ ህያው ሀብትና የማንነታቸው መገለጫ አድርጎታል። ሹዋሊድን በሐረር የሚኖሩ የብሔረሰቡ አባላት ብቻ ሳይሆኑ በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ሐረሪዎች ጭምር የበዓሉን ቀን ጠብቀው ከያሉበት በመሰባሰብ ያከብሩታል። ክብረ በዓሉ በድሬዳዋ፣ በጉርሱም በተለይ ካለፉት ሁለት አስርተ አመታት ወዲህ በአዲስ አበባም በብሔረሰቡ ተወላጆች ዘንድ እየተከበረ የሚገኝ የሐረሪ ብሔረሰብ ትልቅ የማንነት መገለጫ እሴት ነው። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ምንም እንኳን የሹዋል ጾምን የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ሕዝቦች የሚጾሙት ቢሆንም የሹዋሊድን በዓል እንደሐረሪዎች የሚያከብሩት አለመሆኑ ነው።

> **በሃይማኖቱ የሹዋልን ጾም በተከታታይም ሆነ ነጣጥሎ መጾም ይቻላል። ሁለቱም የአጿጿም ስልት ደረጃቸው እኩል ነው። ይሁንና ከዒድ አልፈጥር በኋላ ያሉትን ስድስት ቀናት በተከታታይ መጾም ግን የበለጠ ዋጋ አለው። እንደሚታወቀው ሴቶች በተፈጥሮ አስገዳጅነት ምክንያት በረመዳን የጾም ወቅት የወር አበባ በሚያዩባቸው ቀናት ጾሙን ለማቋረጥ መገደዳቸው አይቀሬ ነው። ይህን ያቋረጡትን ወይም ያጓደሉትን የጾም ቀናትም በሹዋል ጾም ማካካስ ይጠበቅባቸዋል**

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2 ብሔሮችና ብሔረሰቦች ባህላቸውን የመግለጽ፣ የማዳበር፣ የማሳደግና በዘላቂነት የመንከባከብ መብት መረጋገጡ ይታወቃል። 139 የሐረሪ ሕዝብ ክልል ህገ መንግስትም የሐረሪ ብሔረሰብ ታሪኩንና ባህሉን የማልማትና የማበልፀግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀምና የማሳደግ ህጋዊ መብት የተጎናጸፈ መሆኑ ተደንግጓል። በዚህም መሠረት በአዋጅ ቁጥር 61/1999 የሹዋሊድ በዓል የሚከበርበት ዕለት በክልሉ የበዓል ቀን ሆኖ እንዲከበር በአዋጅ ተደንግጓል። ይህም በዕለቱ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ዝግ ሆነው በዓሉ በየዓመቱ በድምቀት እንዲከበር ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ክብረ በዓሉም በብሔረሰቡ አባላትና በሌሎችም አካባቢ ማኀበረሰቦች ዘንድም እንዲታወቅ ምክንያት ሆኗል፡፡በዚህም መነሻነት ቅርሱ የተለያዩ የዓለም ሕዝቦች የመነጋገሪያ እና የመወያያ ርዕስ እንዲሆንና ከሹዋሊድ በዓል እሴቶች ሌሎች ሕዝቦችም ልምድ መቅሰም እንዲችሉ ቅርሱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስመዝገብ አስፈልጓል።

**የሹዋሊድ በዓል አከባበር ሂደት**

የሹዋሊድ በዓል በሐረሪ የሚከበረው ለሶስት ተከታታይ ቀናት ነው። ሐረሪዎች በዓሉ የማንነታቸው መገለጫ ባህላቸው መሆኑን ለመግለጽ ዚኢኛ ኢድ (የኛ በዓል)፣ አዳ ኢድ (የባህል በዓል ወይም ባህላዊ ይዘት ያለው በዓል)፣ ሹዋል ኢዴ በማለት ይጠሩታል። በሹዋሊድ የበዓል አከባበር ወቅት በሚዜሙ ዜማዎች ውስጥ ዚኢኛ ኢድ፣ ሹዋል ኢዴ የሚሉትን ሐረጋት ይደጋግሙታል። በሌላ በኩል አዳ ኢድ (የኛ የሐረሪዎች በዓል) እያሉም ያዜሙበታል። ሹዋሊድ መሠረቱ ሃይማኖት ቢሆንም እንደ ሐረሪ በዓሉ በባህላዊ ክንዋኔዎችና ሥነ-ሥርዓቶች ታጅቦ በደመቀ ሁኔታ የሚከበር ነው (ዙሄር)።

ሹዋሊድን ከሐረሪዎች በተጨማሪ ሌሎች በሐረርና በአካባቢዋ የሚኖሩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ወደ ከተማዋ በመምጣትና በበዓሉ ላይ በመሳተፍ በጋራ የሚተገብሩትየ ማይዳሰስ ቅርስ ነው።

አንዳንዶች አብሮ በመኖርና የአካባቢውን ባህል ከመልመድ የተነሳ የበዓል ሥነ-ሥርዓቱን ከመሳተፍ ባለፈ በአንዳንድ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ በትግበራ የሚሳተፉበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ ዝክሪ በማውጣትና ከበሮ በመምታት በመሳሰሉት ተሳትፎ ያደርጋሉ። የሹዋሊድ በዓል የአካባበር ሥነ-ሥርዓት የሚጀምረው ከሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ማለትም ከሹዋል ወር ስድስተኛው ቀን ምሽት ላይ እስከ የሹዋሊድ ዕለት ከሚውልበት ስምንተኛው ቀን ድረስ ይቀጥላል። በስድስተኛው ቀን ምሽት ሶስት ሰዓት ላይ አባቶችና እናቶች ዝክሪ በማድረግ ማለትም ፈጣሪያቸውን አላህን፣ ነብዩ መሐመድንና በማስታወስና በማወደስ በዓሉን ያከብራሉ። በሚቀጥለውም ምሽት ይኸው ሥነ-ሥርዓት ይቀጥላል። ዋናው የበዓሉ ሥነ-ሥርዓት የሚጀምረው በዋዜማው ምሽት እና በሹዋሊድ በዓል ዕለት ነው (ዲኒ ረመዳን)። በዓሉ በዋነኝነት በሁለቱ የጁገል መግቢያ በሮች በሚገኙ አዋቾች ይከበራል። ይኸውም በሐረር ከተማ በስተምስራቅ የሚገኘው አርጎ በሪ (ኤረር በር) አጠገብ በሚገኘው አው ሹሉም አህመድ አዋች ላይ እና በሐረር በስተሰሜን በኩል አስሱም በሪ (ፈላና በር) አቅራቢያ በሚገኘው አውዋቅበራ አዋች ላይ በጋራ ይከበራል።

በእነዚህ ምሽቶች የሹዋሊድ በዓል የዋዜማ ሥነ-ሥርዓት በአዋቹ ግቢ ይከናወናል። በመጨረሻው የዋዜማ ቀን ሁሉም የሚሳተፍበት በመሆኑ ሰፊ የበዓል ማክበሪያ መድረክ ይዘጋጃል። የሥርዓቱ መሪዎች ወይም ሙሪዶች፣ አባቶችና እናቶች በመድረኩ ላይ ሆነው በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ። ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ ዙሪያቸውን በመሰባሰብ ሥርዓቱን መከታተል በሚችሉበት ሁኔታ ቆመው አለያም ተቀምጠው ይከታተላሉ፡፡

በእነዚህ የዋዜማ ቀናት የአካባቢው ታዳጊ ህፃናት ለዋዜማው ሥነ-ሥርዓት ማድመቂያ የሚገለገሉበት ትንሽና ትልቅ ከረቡ (ከበሮ) የተፈለገውን ድምጽ እንዲያወጣ በእሳት መሞቅ ስላለበት በየቤቱ እየዞሩ እንጨት ያሰባስባሉ። በዚህም ጊዜ የሚከተለውን ዜማ ያዜማሉ።

**በሐረሪኛ ፡- ወዚዞው በሐሬይ**

አው አባድርሌ ኢስሓት አሐድ ኢንጪ

ዳኢም አመትዞም ያቦርደኹ...በማለት ያዜማሉ፡፡

በአማርኛ ሲመለስ፡-

በሠፌው መጥተናል

ለአው አባድር አንድ አንድ እንጨት

ዓመት ዓመት ያድርሳችሁ እንደማለት ነው፡፡

በዚህ መልኩ ታዳጊዎቹ የተፈለገውን እንጨት ከአሰባሰቡ በኋላ ወደ አዋቹ ይገባል። ከዚያም የተዘጋጁትን ከበሮዎች በእሳት የማሞቅ ሥራ ይከናወናል።

ከዚህ በኋላ የበዓሉ እድምተኞች ወደ አዋቹ ገብተው በተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲቀመጡ ይደረጋል። ከበሮውንም የሚመቱት የዓመታት ዕውቀት ልምድና ክህሎት ያካበቱ አዛውንቶች እና ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣውን ዕውቀት የቀሰሙ ወጣቶች ናቸው። ከበሮ መቺዎቹ መጀመሪያ ድምጹን በመቃኘት የተስተካከለ መሆኑን ያረጋግጡና ለበዓሉ ሥነ-ሥርዓት ዝግጁ ያደርጋሉ።

ዕለተ በዓሉ ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ የተጀመረው የዋዜማ ሥነ-ሥርዓት የሚጠናቀቅበት በመሆኑ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ውዳሴዎችና ባህላዊ ጭፈራዎች ታጅቦ በደማቅ ሁኔታ ይከበራል። በዚህ በዓል ላይ ለሥነ-ሥርዓቱ ማድመቂያ የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ይውላሉ። ከእነዚህም መካከል ትንሽና ትልቅ ከረቡ ወይም ከበሮ አንዱና ዋናው ሲሆን ከቁርጥራጭ ጣውላ ከእንጨት የተሰራ በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ከበል›› በመባል የሚታወቀው የእጅ ማጨብጨቢያ እና የከበሮ መምቻ ዱላ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እንደውዳሴው የዜማ ይዘትና የጭፈራ ዓይነት የተለያዩ የዓመታት ስልቶችን በመከተል የተለያዩ ድምጾችን ለማውጣት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ሲሆን ለበዓሉ አከባበርም ልዩ ድምቀት ይሰጣሉ። የምሽቱ የበዓል ሥነ-ሥርዓት የሚጀመረው በአባቶች ምርቃት ነው። ከዚያም ዝክሪ ወይም የምስጋና ዜማ ይቀጥላል። ዝክሪው ‹አዋዮው ሰላም አዋዮው ሰላም ሰላም› በሚል የዜማ ስልት ያለው ነው። በዚህ ሂደት የሴቶች ሚና ዝክሪውን መቀበል፣ በጭብጨባ እና በእልልታ ሥነ-ሥርዓቱን ማድመቅ ይሆናል። ወንዶቹ ደግሞ በተቀመጡበት ከግራ ወደቀኝ አንገታቸውን በማንቀሳቀስ ከፍ ዝቅ የሚለውን የዜማ ስልት እየተከተሉ በመቀበል እየደገሙ ማዜም ነው። የዜማ ስልቱም ‹አዋዮው አዋዮው ሰላም › የሚል ሲሆን፣ ይህም መሀመድ እንዴት ነህ! ሰላም ባንተ ይውረድ እንደማለት ነው። በዚህ ሂደት የበዓሉ ተሳታፊዎች ከአንዱ አዋች ወደሌላኛው አዋች የበዓል ሥነ-ሥርዓቱ ወደደመቀበት እየተመላለሱ ያከብራሉ፡፡

# ሳምንቱን በታሪክ

## ዳግማዊው ድል

**ዋስልኝ አየለ**

ባለፈው ሐሙስ የአርበኞች ቀንን አክብረናል። ይህ የአርበኞች ቀን በጀግኖች አባቶቻችን ተጋድሎ ዳግም የተገኘ ድል ነው። በዓድዋ ጦርነት ሽንፈት የተከናነበው ጣሊያን ለ40 ዓመታት ያህል ዝግጅት አድርጎ ዳግም ወረራ ፈጽሟል። ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በለመዱት የጀግንነት ስልትና ወኔ ባደረጉት ተጋድሎ ሉዓላዊነታቸውን አስከብረዋል። በዛሬው የሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ይህን ኢትዮጵያውያን ፋሽስት ጣልያንን ድል ያደረጉበትን የድል ቀን እናስታውሳለን።

የተክለ ጻድቅ መኩሪያ «የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ» የባህሩ ዘውዴ «የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983» መጽሐፎችን እና የተለያዩ ድረ ገጾችን በምንጭነት ተጠቅመናል።

ኢትዮጵያ ከ81 ዓመታት በፊት በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ሰንደቅ ዓላማዋ ከታጠፈ፣ ሉዓላዊነቷ ከተደፈረ 5 ዓመታት በኋላ በጠላቷ ፋሽስት ጣልያን ላይ ድል የተቀዳጀችው ሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በ11 ሰዓት ንጉሰ ነገሥቱ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ በአርበኞች ብርታትና መስዋዕትነት የፋሽስት ጣሊያንን ባንዲራ አውርደው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በታላቁ ቤተ መንግሥት ሲሰቅሉ ነው፡፡

የሚያዝያ 27 የንጉሰ ነገስቱ አዲስ አበባ ገብቶ ሰንደቅ ዓለማ መስቀል ሌላው ታሪካዊነቱ ከአምስት ዓመታት አስቀድሞ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 በዚያው ቀን ወደ ኢትዮጵያ የዘመተው የጣልያኑ ጦር አዛዥ ጄኔራል ባዶሊዩ አዲስ አበባ ገብቶ በታላቁ ቤተ መንግሥት የጣሊያንን ባንዲራ የሰቀለበት ቀን መሆኑ ነው፡፡ ጣሊያን ከዓድዋ ሽንፈቷ 40 ዓመታት በኋላ በዘመናዊ የጦር መሣሪያና በወታደራዊ ኃይል ይበልጥ ተደርጅታ ኢትዮጵያን ከሦስት አቅጣጫዎች ወረረች፡፡ ከዓድዋው ዘመቻ ያልተሻለ የጦር ትጥቅ የነበራት ኢትዮጵያም የጣሊያንን ጦር በፅናት ተዋጋች፡፡

የወቅቱ ሃያላን አገሮች እንግሊዝና ፈረንሳይ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ በግዢ እንዳታገኝ ለጣሊያን ተደርበው ስላሴሩባት ኢትዮጵያ ብቻዋን ጦርነቱን በመጋፈጧ ድል ማግኘት አልቻለችም፡፡ የየግንባሮቹ የኢትዮጵያ የጦር አዛዦች ብዙዎቹ ሞተው ሠራዊቱም በመርዝ ጋዝና በአውሮፕላን ቦምብ ተደብድቦ ያለቀው አልቆ የቀረው ቀርቶ ጣልያን ጊዜያዊ ድል አግኝታ ዋና ዋና ከተሞችን ብትቆጣጠርም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በገጠሩ ክፍል እምቢ ለነፃነቴ ፤ እምቢ ለአገሬ ብለው የሽምቅ ውጊያ ጀመሩ።

ንጉሰ ነገስቱም ስደት ሄደው በጊዜው ለነበረው የመንግሥታቱ ማህበር(ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) አቤቱታ አቀረቡ። የሚሰማቸው ግን አላገኙም። የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ከቀን ወደ ቀን ድል እየተቀዳጁ የጣሊያን ወታደሮችን መፈናፈኛ፤ መግቢያ መውጫ አሳጧቸው። ከጣሊያን ወታደሮች ይማርኳቸው በነበሩ መሣሪያዎች ራሳቸውን እያደራጁ አብዛኛውን የገጠር ክፍል ተቆጣጠሩት።

በዚህ መሃል እንግዲህ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀስ ለኢትዮጵያ ትልቅ ቦታ ነበረው። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲቀሰቀስ ጣሊያን የናዚ ጀርመን አጋር ሆነች። ያን ጊዜ እንግሊዞች የጣሊያን ጠላት ሆነው ኢትዮጵያን መደገፍ ጀመሩ።



**ጀግናች ኢትዮጵያውያን የፋሽስት ጣልያንን ወራሪ ሀይል ድል ያደረጉበት ሚያዚያ 27 ቀን በየአመቱ እየታሰበ ነው**

ወታደራዊ ድጋፍ ሰጥተው፤ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ረዷቸው፡፡ በጄኔራል ካኒንግሂም የሚመራው የእንግሊዝ ጦር ከኬንያ ተነስቶ በደቡብ አቅጣጫ ወደ መሀል ኢትዮጵያ ሲገሰግስ፤ በጄኔራል ፕላት የሚመራው ጦር ከሱዳን ተነስቶ ወደ አሥመራ ፤ ከዚያም በሰሜን አቅጣጫ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ተንቀሳቀሰ፡፡

በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ የሚመራውና የአርበኞችና የእንግሊዝ አማካሪዎች የሚገኙበት «ጌዲዮን» ተብሎ የተሰየመው ጦር ከሱዳን ተነስቶ በኦሜድላ አልፎ በጐጃም በኩል ወደ መሐል አገር ገሠገሠ።

በመካከለኛው ኢትዮጵያ አርበኞች በጣሊያን ወታደሮች ላይ ጥቃታቸውን አፋፋሙ፡፡ ጣሊያኖች ክፉኛ ተሸነፉ። በየቦታው ድል የመሆናቸው ዜና ናኘ። ዘመቻው ከተጀመረ ሁለት ወራት ሳይሞላው ፤ ጣሊያኖች አዲስ አበባን ለቀው ፈረጠጡ፡፡

መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም የጄኔራል ካኒንግሃም ጦር አዲስ አበባን ተቆጣጠረ፡፡ እንግሊዞች ኢትዮጵያውያን አርበኞች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ስላልፈለጉ ቀዳማዊ አጼ ኃይል ሥላሴን በደብረ ማርቆስ ለአንድ ወር ያህል እንዲቆዩ አደረጓቸው። ይሁንና በአዲስ አበባ በአርበኞች ተፅዕኖና ቅሬታ የተነሳ አርበኞች ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ ፈቀዱ። አፄ ኃይለ ሥላሴም ወደ አዲስ አበባ እንዲጓዙ ፈቀዱ። ንጉሰ ነገስቱም አዲስ አበባ በታላቁ ቤተ መንግሥት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ሰቀሉ።

አዲስ አበባ ገብተው «ይህ የምትሰሙት ድምጽ የኔ የንጉሳችሁ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው። አባቶቻችን ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው በነፃነት ያቆዩልን አገራችንን ወደ ከፍተኛው የሥልጣኔ ደረጃ ለማራመድ የምንደክምበት ጊዜ ከጥንት ጀምሮ ስለሆነ ደመኛ ጠላታችን ኢጣሊያ ይህንን እይታ ወሰናችንን ጥሳ የግፍ ጦርነት እንዳደረገችብን ሁላችሁም የምታውቁት ነው። እኛም በተቻለን ከተከላከልን በኋላ እርዳታ ለመጠየቅ ወደ መንግስታቱ ማህበር ወደ ወዳጆቻችን መንግስታቶች መጣን፤ እዚህ ስንነጋገር በቆየንበት ጊዜ የኢትዮጵያ አርበኞች ሰይፋችሁን ሳትከቱ ፊታችሁን ሳትመልሱ ሰንደቅ አላማችሁን ሳታጥፉ ለባዕድ አንገዛም በማለት በመሳሪያ ብዛት ከሚበልጣችሁ ጨካኝ ጠላት ጋር የባሕርይ የሆነውን ጀግንነታችሁን መሣሪያ አድርጋችሁ በኢትዮጵያ አምላክ ብቻ ተማምናችሁ በጀግንነት ቀንና ሌሊት በዱር በገደል ስትጋደሉ ቆይታችሁ ይኸው አሁን እንደምታዩት የማያቋርጥ የአምስት አመት ትግላችሁ የድካማችሁንና የመሥዕዋታችሁን ፍሬ ለማየት እንድትበቁ አደረጋችሁ፡፡

**የአገሬ የኢትዮጵያ ህዝብ!**

ዛሬ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታ እልል እያለች ምስጋናዋን የምታቀርብበት ደስታዋንም ለልጆቿ የምትገልጽበት ቀን ነው። የኢትዮጵያ ልጆች ከባድ የመከራ ቀንበርና ከዘለዓለም ባርነት ነፃ የወጡበት ቀንና እኛም አምስት አመት ሙሉ ተለይተነው ከነበረው ከምንወደውና ከምንናፍቀው ሕዝባችን ጋር ለመቀላቀል የበቃንበት ቀን ስለሆነ ይህ ቀን የተከበረና የተቀደሰ በያመቱም ታላቁ የኢትዮጵያ በዓል የሚውልበት ነው። በዚህም ቀን ለሚወዷት ላገራቸው ነፃነት ለንጉሰ ነገስታቸውና ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር ካባቶቻቸው የተላለፈውን ጥብቅ አደራ አናስዎስድም በማለት መስዋዕት ሆነው ደማቸውን ያፈሰሱትን አጥንታቸውን የከሰከሱትን ጀግኖቻችንን እናስታውሳለን። ለዚህም ለጀግኖቻችን የኢትዮጵያ ታሪክ ምስክር ይሆናል።

ባለፈው አምስት አመታት ውስጥ በዝርዝር ተነግረውና ተቆጥረው የማያልቁ ያገኙናቸው መከራና ስቃይ ትምህርት ሆነውን ሰራተኛነት አንድነት ህብረትና ፍቅር በልባችሁ ተጽፈው ለምናስበው ለኢትዮጵያ ጉዳይ ረዳቶች ለመሆን ዋና ትምህርት የሚሰጣችሁ ነው። ባዲሷ ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲያ የማትነካጠሉ በሕግ ፊት ትክክልና ነፃነት ያላችሁ ሕዝቦች እንድትሆኑ እንፈልጋለን። አገር የሚለማበትን ሕዝብ የሚበለጽግበትን እርሻ፣ ንግድ፣ ትምህርትና ጥበብ የሚስፋበትን የሕዝባችን ሕይወቱና ሀብቱ የሚጠበቅበትን የአገር አስተዳደርም ባዲሱ ስልጣኔ ተለውጦ ፍጹም የሚሆንበትን ይህን ለመሰለው ለምንደክምበት ስራ አብሮ ደካሚ መሆን አለባችሁ» ሲሉ አስገንዝበዋል።

ይሄ የኢትዮጵያውያን የድል ብስራት የሆነው የአርበኞች ቀን ከፍተኛ ዋጋ የተከፈለበት ነው። በዚህ ጦርነት ውስጥ ምላጭ ስቦ ጥይት ከተኮሰው አርበኛ በተጨማሪ በየቤቱ ሆኖ የተባበረውም ቀላል አልነበረም።

ሰራዊቱ «ደረቅ ጦር» እና «መደዴ ጦር» ተብሎ ለሁለት ተከፍሎም ነበር። ደረቅ ጦር የተባለው ሙሉ በሙሉ ውጊያ ላይ የሚያተኩር ሲሆን «መደዴ ጦር» የተባለው ደግሞ እንደሁኔታው የእርሻ ሥራ ላይ እንዲሰማራ ይደረጋል። ነገሩ ሲከፋ ግን አርበኞች ፍራፍሬ፣ ቅጠላቅጠልና የዱር አውሬ ሁሉ እየበሉ ተዋግተዋል። እናቶች ከሰራዊቱ ጋር አብሮ በመዝመት ምግብና ውሃ ከማቀበል በተጨማሪ ባህላዊ ህክምና እየሰጡ ሰራዊቱን ታድገዋል። የወደቀውን በማንሳት የቆሰለውን በመጠገን ተሳትፈዋል።

ይህ የአርበኞች ቀን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የተጋድሎ ድል ነው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያውያን ይህንና ኢትዮጵያውያን በወራሪዎችና ተላላኪዎቻቸው ላይ በየጊዜው የተቀዳጁቸውን ድሎች ሁሌም ያስቧቸዋል።

## የውጫሌ ውል 133ኛ ዓመት

በዚህ ሳምንት የሚታወሰው ሌላኛው ክስተት ከ133 ዓመታት በፊት ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም የተፈረመውና ለዓድዋ ጦርነት ሰበብ የሆነው የውጫሌ ውል ነው።

የውጫሌ ውል በአሁኗ አምበሳል ወረዳ ውጫሌ በምትባል ቦታ በአጼ ምኒልክና በጣሊያኑ ንጉስ ኢምቤርቶ ተወካይ ኮንት አንቶሎኒ መካከል ተፈረመ። ውሉ 20 አንቀጾች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ አንቀጾች ውስጥ ሰበበኛዋ አንቀጽ 17 ለጣሊያን የውርደት ካባ ያለበሰውን የዓድዋን ጦርነት አስከተለች፤ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ ድል በማጎናጸፍ የጥቁርን ጀግንነት ያስመሰከረ ክስተት ሆነች።

አንቀጽ 17 በአማርኛ «የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ከአውሮፓ ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል» የሚል ሲሆን፣ ቀጥተኛ ትርጉሙም የኢትዮጵያ መንግስት ከፈቀደ ወይንም ከፈለገ በኢጣሊያ በኩል ከውጭ መንግስታት ጋር ግንኙነት ማድረግ እንደሚችል የሚጠቅስ ነው፡፡

የአንቀጹ የጣሊያንኛ ትርጉም ግን «የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ አገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካኝነት ማድረግ ይገባዋል» የሚል ነበር። ይህም የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት በቀጥታ በጣሊያን በኩል እንዲከናወን የሚያስገድድ ተደርጎ የሰፈረ ነው፡፡

በአንቀጽ 17 አማካኝነት ጣሊያን የውሉን ሀሳብ በጣሊያንኛ በመቀየር የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በመገርሰስ የጣልያን ሞግዚት እንድትሆን ቀዳዳ እያበጀች ነው ብለው ነገሥታቱ እና መኳንንቱ ስለተገነዘቡ የውጫሌ ውልን እንደማይቀበሉት አሳወቁ።

የጣሊያን መንግስት ውሉን ለማፍረስ አሻፈረኝ በሚልበት ጊዜ፣ የውጫሌ ውል እንዲፈርስና ኢትዮጵያ ለማይቀረው ጦርነት እንድትዘጋጅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ባለቤት እቴጌ ጣይቱ ብጡል እንደነበሩ ታሪክ ያመለክታል።

እቴጌዋ «እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም። ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከምቀበል ጦርነት እመርጣለሁ» ብለው ነበር። በወቅቱ «ይስሙ ንጉሥ!» የሚል ታሪካዊ ንግግር አድርገዋል። ይህን ንግግራቸውን ተከትሎም በደቡብ ወሎ ዞን አምባሰል ወረዳ የሚገኘውና የውጫሌ ውል የተፈረመበት ቦታ «ይስማ ንጉሥ» የሚል ስያሜ አግኝቷል።

ይህ ታሪካዊ ቦታ የባህል ማዕከል ተገንብቶለት የቱሪዝም መዳረሻ ሆኗል። የባህል ማዕከሉ የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያሳዩ መረጃዎችን ያካተተ ሲሆን፣ የቀለም ቅቡም አሸናፊነትና ተሸናፊነትን እንዲወክል በነጭና ጥቁር ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። በማዕከሉ ጣሪያ ላይ አሸናፊነትን የሚያመለክት የእጅ ምልክት ተሰርቷል። በ25 ሚሊየን ብር የተገነባው ይህ ባህል ማዕከል፤ የመግቢያ በሩ የኢትዮጵያ ቁጥር ፲፯ (17) ተጽፎበታል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ


## አሊ አብደላ ኬይፋ እንዴት ሙዚቃ አሳታሚ ሆነ

እ.ኤ.አ ሰኔ 19 ቀን 1942 ዓ.ም፤ የአባጅፋር አገር ጅማ ከተማ፤ የኦሮሞ ብሔር አባል ከሆኑት ኢትዮጵያዊ እናቱና ከየመናዊ አባቱ ተወለደ ፤ ዓሊ አብደላ ኬይፋ። በልጅነቱ ከጅማ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ጣልያን ሰፈር የመጣው ዓሊ፣ መርካቶ አካባቢ በሚገኘው የመን ማህበረሰብ ትምህርት ቤት በመግባት የአረብኛ ቋንቋ መማር ጀመረ። በዚህ ት/ቤት ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገባ።

ከልጅነቱ ጀምሮ እግር ኳስ መጫወት በጣም ይወድ ነበርና ለትምህርት ቤቱና ሀረር መስፍን ተብሎ ይጠራ ለነበረ የእግር ኳስ ቡድን፤ በመቀጠልም በጊዜው ተወዳጅና ታዋቂ ለነበረው ለቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ቡድን ተሰልፎ ተጫውቷል፡፡

ዓሊ ገና የ14 ዓመት ታዳጊ እያለ ነበር የእንጀራ አባቱ ከጅማ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ቡና እየላኩለት ይሸጥ ነበር። ታዳጊው ዓሊም ለበርካታ ጊዜያት የቡና ንግዱን ካከናወነ በኋላ የእራሱን ንግድ መጀመር በሚያስብበት ጊዜ ወላጅ እናቱ በአስገራሚ ሁኔታ የንግድ መነሻ ገንዘብ እገዛ እንዴት እንዳደረጉለት ሲናገር። "የራሴን ንግድ ስራ ለመጀመር የቻልኩት ወላጅ እናቴ በወቅቱ የነበራትን የወርቅ ቀበቶ ሸጣ መነሻ የሚሆነኝን ገንዘብ ስለሰጠችኝ ነው፡፡" ብሏል። በዚህ ገንዘብ ዓሊ ቺፖሊኒ ተብሎ ይታወቅ የነበረ ከአስመራ ከተማ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ ሽራ ጫማ ብቸኛ ወኪል በመሆን ያከፋፍል ነበር።

ዓሊ ለስድስት ዓመታት ያህል ብቸኛ ወኪል በመሆን የቺፖሊኒ ጫማ ሲያከፋፍል ከቆየ በኋላ የሶኒ /Sony/ ምርት የሆኑ እንደ ሬዲዮ፣ ቴፕ ሪከርደር፣ ቴሌቪዥን፣ የሶኒ ካሴቶች የመሳሰሉ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ማከፋፈል ጀመረ። በዚህ የሶኒ ምርቶች ማከፋፈል ሥራ ላይ ተሠማርቶ በነበረበት ወቅት ዓሊ ሪል ቴፕና ካሴት የሚያጫውት ሪከርደር ነበረው፡፡



**አሊ አብደላ ኬይፋ (አሊ ታንጎ)**

ከዕለታት በአንዱ ቀን አንድ የማይታወቅ ግለሰብ ይህንን ሪከርደር በዱቤ ሸጥልኝ ብሎ ይጠይቀዋል። ዓሊም "ምንም ችግር የለም" በማለት ቴፑን በ3000 ሺህ ብር በዱቤ ይሰጠዋል። ሆኖም ግን ግለሰቡ እዳውን ሳይከፍል እልም ብሉ ይጠፋል።

ከተወሰነ ጊዜያት በኋላ ይህ ዱቤ ሳይከፈል የቀረው ግለሰብ በመሐል ፒያሣ ካሊፕሶ ሙዚቃ ቤት መጨረሻ ፋሽን እና አንድ መጽሐፍ ቅዱስ መሸጫ መደብር በአጠቃላይ ሦስት ሱቆች እንዳሉት አሊ በመረዳቱ ወደ ግለሰቡ ሱቅ ሄዶ እዳውን እንዲከፍለው ሲጠይቀው ግለሰቡ እዳውን ለመክፈል ባለመቻሉ ካሊፕሶ ሙዚቃ ቤት በሚባለው የንግድ ቤቱ ተደበቀ። ተደብቆም አልቀረም፤ ከዓሊ ዓይን ለማምለጥ ሳይችል ቀረ፡፡

ከዚያም "ዓሊ ገንዘቡን ለምን አትከፍልም?" ብሎ ቢጠይቀው ግለሰቡም በጊዜው መክፈል እንደማይችል ይነግረዋል። ዓሊ ግን "በቃ ገንዘቤን መክፈል ካቃተህ ይህንን ሱቅ ገንዘብ ጨምሬልህ ለእኔ ስጠኝ!" በማለት 3,000 ሺህ ብር ጨምሮ በአጠቃላይ ስድስት ሺህ ብር ከፍሎ ካሊፕሶ ሙዚቃ ቤትን ወደ ታንጐ ሙዚቃ ቤት በመለወጥ የእራሱ አደረገው።

ዓሊ ካሊፕሶ ሙዚቃ ቤትን የእራሱ ካደረገው በኋላ በሙዚቃ ቤቱ ውስጥ የእንግሊዝኛ፣ ጣልያንኛና የፈረንሣይኛ ሙዚቃ ሸክላዎች ያገኛል። ይህ አጋጣሚ ዓሊ ወደ ሸክላ መቅረፅ ሥራ እንዲገባ አነሳሳው። ከዚያ በኋላ ነው ዛሬም ድረስ የምንሰማቸው የነ አስቴር አወቀ ፤ ሙሉቀን መለሰ ፤ ንዋይ ደበበ፤ አሊ ቢራ፤ መሀሙድ አህመድ ፤ ብዙነሽ በቀለ ፤ ሂሩት በቀለ እና ሌሎች ተወዳጅ ድምጻውያን ካሴቶች እጃችን ላይ ደርሰው በሙዚቃ ሀሴት ያደረግነው፡፡

ታንጎ ሙዚቃ ቤት ካይፋ ሪከርድስ በተለይም ለወጣት ድምፃውያንና ለሌሎችም ዕውቅ ድምፃውያን ከ1973 ዓ.ም. እስከ 1977 ዓ.ም. ብቻ 53 የሚሆኑ የሙዚቃ ሥራዎችን አሳትሞ ለሕዝብ አቅርቧል። እሱ ይህን ሲሰራ ከዝነኛው ሴኮ ሰዓት ጋር ያስተዋወቀው ደግሞ ወንድሙ መሀመድ ነው። ሌላኛው ወንድሙ አህመድ ቡከር ደግሞ እንደ አሊ ኳስ ተጫዋች ሆኖ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እስከ መጫወት ደርሷል።

ታዋቂው የሙዚቃ አሳታሚ አሊ ከአመት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡

## የዜማ ሊቁ ሳህሌ ደጋጎ

ሳህሌ ደጋጎ ኢትዮጵያ በዘመኗ ከምታውቃቸው የዜማ ጠቢባን መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው። ከ500 በላይ የአማርኛ እና ኦሮምኛ ግጥም እና ዜማዎችን ለኢትዮጵያውያን ጆሮዎች አበርክቷል። ከታላላቆቹ ድምጻውያን ጥላሁን ገሰሰ እና ብዙነሽ በቀለ እንዲሁም የነሱ የዘመን አጋሮች የሙዚቃ ስኬት ጀርባ የነበረ ግዙፍ ጥበበኛ ነው። የዛሬው የዝነኞች ገጽ አምዳችንም በዚሁ ጥበበኛ ጋዜጠኛ ወሰንሰገድ ገ/ኪዳን የጻፈውን የአርቲስቱ አጭር ታሪክ ይዘን ቀርበናል፡፡

ሳህሌ ደጋጎ በ1923 ዓ.ም ወለጋ፣ ነጆ በባላምባራስ ደጋጎ አለቤ እና በወ/ሮ ደጊቱ ፈይሳ ቤት ታላቅ ደስታ ሆነ፡- ወንድ ልጅ ተወለደ። እልልታው ቀለጠ።

ነጆ ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ፣ በአንዲት መንደር የተወለደው ይህ ሕፃን፣ በምድረ ኢትዮጵያ ስሙ የገነነ፣ ዝነኛ እና ታላቅ የሙዚቃ ሰው ይሆናል ብሎ የገመተ አልነበረም። እንደማንኛውም ሕፃን በወለጋ ነጆ ምድር እየቦረቀ አደገ። ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ነቀምት ተላከ፡- ት/ቤት ገባ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ወደ አዲስ አበባ አቀና። እናም ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ዘለቀ።

እንደማንኛውም እንደዘመኑ ተማሪዎች እውቀት የተጠማ ነው። ንቁ ነው። ጎረምሳ ነው። በዚያ የጉርምስና ዕድሜው የሚያያቸው ወታደሮች ትኩረቱን ሳቡት። ሸንቃጦች ናቸው። አለባበሳቸው ያምራል። እነሱን መሆን አማረው። በውትድርና ፍቅር ተለከፈ። እናም ሄደ፡- ወደ ክቡር ዘበኛ ክ/ጦር። ተቀጠረ። በ19 ዓመቱ፡- በ1942 ዓ.ም።

የተቀጠረው በተራ ወታደርነት ነው። ስልጠና ወሰደ። ለውትድርና ፍቅር ስለነበረው ስልጠናው አልከበደውም። ከስልጠና በኋላ ክቡር ዘበኛ ሙዚቃ ክፍል ውስጥ ተመደበ። እግረኛ ባንድ ውስጥ።

የእግረኛ ባንዱ አሰልጣኝ ፈረንሳዊ ነው። ሙሴ ኒኮ ይባላል። ክላርኔት የተባለ የሙዚቃ መሳሪያ ሰጠው። በሚገባ አሰለጠነው። ሳህሌ ጎበዝ ነው፤ ክላርኔትን ተራቀቀባት። ቀጠለ። አኮርዲዮንን፣ አልቶ ሳክስን፣ ፒያኖን ተካነባቸው። ድንቅ የሙዚቃ ባለሙያ ወጣው።

በውትድርናውም እንደዚያው ነው። ጥንቁቅ ነው። ስነ ስርዓት አክባሪ ነው። በዚህም የተነሳ በአንድ ጊዜ ከተራ ወታደርነት ተንደርድሮ የሃምሳ አለቅነት ማዕረግ ተቀዳጀ።

**ኮ/ል ሳህሌ ከ500 በላይ ሙዚቃ አቀናብረዋል። እጅግ ብዙ ግጥምና ዜማ ፅፈዋል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ከ100 በላይ የኦሮምኛ ዜማና ግጥምም አበርክተዋል፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ዘመን አይሽሬ አሻራ ያሳረፉ ጎምቱ ባለሙያ ናቸው**

"ጠቅል ሬዲዮ ጣቢያ" በ1950ዎቹ መጀመሪያ ነው የተቋቋመው። ወታደራዊ ሬዲዮ ጣቢያ ነው። ሙዚቀኞች ለሕዝብ በቀጥታ ሙዚቃቸውን የሚያቀርቡበት ጣቢያም ነበር፡- በወቅቱ።

ይህ ጣቢያ በተቋቋመ ጊዜ በአኮርዲዮን ጥዑም ዜማ ለጣቢያው አድማጮች ሲያንቆሩ ከነበሩት የሙዚቃ ሰዎች መካከል የመጀመሪያው ነበር፡- ሣህሌ ደጋጎ።

ከዚያም፣ ከእነ ሻለቃ ግርማ ይህደጎ፣ ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስ እና ከሻለቃ ባሻ ገብረአብ ጋር የክብር ዘበኛ ኦርኬስትራን ደመቀባት። ሙዚቃ ቀማሪ፣ ዜማና ግጥም ደራሲ፣ እንደዚሁም የባንድ ኃላፊ በመሆን፣ በዝና ላይ ዝና፣ በክብር ላይ ክብር እየጨመረ ሄደ። በማዕረግም አደገ፤ ተመነደገ። የኮሎኔልነት ማዕረግም ተቀዳጀ።

ከዚህ በኋላ "አንቱ" እያልን ነው ታሪኩን የምንተርከው። በስራዎቻቸው በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ መንገስ ከቻሉ ጎምቱ የሙዚቃ ባለሙያዎች ተርታ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸውና።

ብዙዎቻችን ኮ/ል ሳህሌን የምናውቃቸው በሙዚቃ ሰውነታቸው ብቻ ነው። እሳቸው ግን "ሁለገብ የጥበብ ሰው" ነበሩ። የሕይወት ታሪካቸው እንደሚዘክረው አጫጭር እና ረዣዥም ድራማዎችም ይደርሱ ነበር። ከሁሉ በላይ ግን የሚጎላው ሙዚቃ አቀናባሪነታቸው ነው። እንዲያም ሆኖ እጅግ በጣም ብዙ የግጥምና የዜማ ድርሰቶችን አበርክተዋል።

ለአብነት ያህል፡- ጥላሁን ገሠሠ ከተጫወታቸው ሙዚቃዎች ውስጥ "ስቆ መኖር"፣ "እውነት ማሪኝ" የሚሉት ግጥሞች የኮሎኔል ሳህሌ የፈጠራ ውጤቶች ናቸው። "ዋይ ዋይ ሲሉ"፣ "ውሸት ለመናገር"፣ "ልብሽን ለአፈር ሰው"፣ "ኮቱሜ"፣ የሚሉትን ዘፈኖች ደግሞ ግጥምና ዜማዎች ሰርተዋል።

የድምፃዊት ብዙነሽ በቀለ "አይወጣኝም ክፉ ነገር"፣ "ፍላጎቴ"፣ "ምን ነበር"፣ "ምንድነው ትዝታህ"፣ … የተሰኙትን ዘፈኖች አቀናብረዋል። "ከንቱ ሥጋ" "አታሳየኝ ጭንቁን"፣ "የፍቅር ወጋገን"፣ "ቃልኪዳን"፣ "በብር አይገዛም"፣ "ፍቅርህ ቀሰቀሰኝ"፣ ወዘተ የተሰኙትን ዜማና ግጥሞች አበርክተዋል።

ከመሐሙድ አሕሙድ፣ ከተፈራ ካሳ፣ ከመንበረ በየነ ፤ ከውብሻው ስለሺ እና ስማቸውን ያልጠቀስናቸው አንቱ የተባሉ ድምፃውያን ጀርባ ሕዋው አሻራቸውን ያሳረፉ ድንቅ ባለሙያ ነበሩ፡- ኮ/ል ሳህሌ።

ኮ/ል ሳህሌ ከላይ ለጠቀስናቸው እና ለሌሎች ብዙ ሙዚቀኞች ከ500 በላይ ሙዚቃ አቀናብረዋል። እጅግ ብዙ ግጥምና ዜማ ፅፈዋል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ከ100 በላይ የኦሮምኛ ዜማና ግጥምም አበርክተዋል፤ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ታሪክ ውስጥ ዘመን አይሽሬ አሻራ ያሳረፉ ጎምቱ ባለሙያ ናቸው/ነበሩ፡- ኮ/ል ሳህሌ ደጋጎ።

እኚህ ታላቅ እና ጎምቱ የሙዚቃ ባለሙያ ባደረባቸው ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በ79 ዓመታቸው ነው። ቀኑም መጋቢት አምስት ቀን 2002 ዓ.ም።




# ልጆች፣ የንባብ ባህል እንዴት ማዳበር ይችላሉ?

**አስናቀ ፀጋዬ**

ልጆች እንዴት ናችሁ? ባለፈው ሳምንት በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት ለማምጣት ምን አይነት የአጠናን ዘዴ መከተል እንዳለባችሁ ነግሬያችሁ ነበር። የነገርኳችሁን የአጠናን ዘዴዎች ተግባራዊ እያደረጋችሁ እንደሆነም አምናለሁ። በዚህም ጥሩ ውጤት እንደምታመጡ እተማመናለሁ።

ለመሆኑ ልጆች ከመማሪያ መጻሕፍቶቻችሁ ውጭ ሌሎችን ታነባላችሁ? የምታነቡስ ከሆነ ምን አይነት መጻሕፍትን ነው የምታነቡት? ይህን ጥያቄ ያለ ምክንያት አይደለም ያነሳሁት። ምክንያቱም ልጆች በአገራችን የንባብ ባህል እምብዛም ስላልዳበረ ነው።

እናንተም ብትሆኑ በአብዛኛው የመማሪያ መጻሕፍትን እንጂ ሌሎችን ዘወትር ታነባላችሁ ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል። ይህን ስል ግን ሁላችሁንም አይደለም። ጥሩ የንባብ ልምድ ያላችሁ ልጆች እንደምትኖሩም አውቃለሁ።

ታዲያ ልጆች የማንበብ ልምድ ገና በልጅነት ነውና የሚጀምረው ይህንን ልምድ ከወዲሁ ማዳበር አለባችሁ። ጠንካራ የንባብ ባህል ካላችሁ ወደፊት የእውቀት ደሃ አትሆኑም። እዚሁ አገራችሁ ላይ ተቀምጣችሁ ዓለምን መዞር ትችላላችሁ። ለነገሮች ያላችሁ አተያይም ይሰፋል። የእውቀት አድማሳችሁም ይጨምራል።

ልጆች የተሻለ የንባብ ባህል በቤታቸው ማዳበር እንዲችሉ የሚከተሉትን ስምንት መንገዶች መከተል በቂ ስለመሆኑ የመስኩ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ወላጆችም እነዚህን መንገዶች ተከትለው የልጆቻቸው የንባብ ባህል እንዲዳብር ማድረግ እንዳለባቸው ይመከራሉ።

**1ኛ. ንባብ የእለት ተእለት ልምዳቸው እንዲሆን እርዷቸው**

ልጆች ንባብን የእለት ተእለት ልምዳቸው ካደረጉ ልተወው ቢሉ እንኳን አይችሉም። ምክንያቱም ማንበብ ዘወትር ጠዋት ተነስተው ፊታቸውን ታጥበው ቁርሳቸውን



እንደሚበሉት አይነት ልምድ ስለሚሆን ነው። ይህ ልምድ እየዳበረ በሄደ ቁጥር ደግሞ በርካታ መጻሕፍትን የማንበብ አጋጣሚን ይፈጥርላቸዋል። አእምሯቸውም በእውቀት እየዳበረ ይሄዳል። ስለዚህ ልጆች ንባብን የእለት ተእለት ተግባራቸው ማድረግ አለባቸው። ለዚህም የወላጆቻው እገዛ ወሳኝ ነው።

**2ኛ. ልጆቻችሁ ፊት ለፊት አንብቡ**

ልጆች ብዙ ግዜ ወላጆቻቸው የሚያደርጓቸውን ነገሮች ነው መልሰው የሚያደርጉት። ወላጆች መልካም ነገሮችን ልጆቻቸው ፊት ባደረጉ ቁጥር ልጆችም መልሰው መልካም ተግባሩን ይደግሙታል። ከዚህ በተቃራኒ ልጆች ወላጆቻቸው መጥፎ ነገሮችን ፊት ለፊታቸው ሲያደርጉ ይህንኑ የመድገም እድልቸው የሰፋ ነው።

ስለዚህ ወላጆች ልጆቻችሁ የንባብ ባህልን እንዲያዳብሩ ከፈለጋችሁ እናንተ አንብባችሁ ለልጆቻችሁ ማሳየት ይኖርባችኋል። ልጆቻችሁ ፊት ለፊት መጽሐፍ ባነበባችሁ ቁጥር ልጆቻችሁ እናንት ያደረጋችሁትን ለማድረግ ይነሳሳሉ። በዚህም ሳያስቡት ከመጻሕፍት ጋር የቅርብ ጓደኞነት ይፈጥራሉ፡፡

**3ኛ. የማንበቢያ ቦታ አመቻቹ**

የንባብ ባህልን ለማዳበር የማንበቢያ ቦታ ለልጆች ወሳኝ ነው። ይህ ሲባል ታዲያ የልጆች ማንበቢያ ቦታ በጣምም ጠባብ በጣምም ደግሞ ሰፊ፤ እንዲሁም በመጻሕፍት በተጨናነቁ ሼልፎች መሞላት አለበት ማለት አይደለም። የማንበቢያ ቦታው ልጆች በሚተኙባቸው ክፍሎች አመቺ ቦታዎች ላይ ሊሆን ይችላል። ዋናው ነገር ግን ክፍሉ ለልጆች ለማንበብ አመቺና በቂ ብርሃን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ ነው።

**4ኛ. ወደ ቤተመጻሕፍት ይውሰዷቸው**

ቤተመጻሕፍቶች አዳዲስ ሀሳቦችን፣ እውቀቶችን ብቻ ሳይሆን፤ አዳዲስ መጻሕፍቶችንና ደራሲዎቻቸውን የመተዋወቂያ ትልቅ ስፍራዎች ናቸው። አብዛኛዎቹም ለልጆች የሚሆኑ መጻሕፍትን ያሟሉ ናቸው። አንዳንዴም ከንባብ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ፕሮግራሞችን ሊያዘጋጁ ይችላሉ። ወላጆች ልጆቻችሁን ወደዚህ የእውቀት ማእከል የምትወስዷቸው ከሆነ መልካም የንባብ ባህል የማዳበር እድል እንዲሰጣቸውና ሌሎች ልጆችም እነሱን አይተው ንባብ እንዲጀምሩ ያስችላቸዋል።

**5ኛ. ልጆች የሚፈልጉትን እንዲያነቡ እድል ይስጧቸው**

ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ቤተመጻሕፍት ሲወስዷቸው እዛ ያሉ መጻሕፍትን ተዘዋውረው እንዲያዩና የሚፈልጉትን መርጠው እንዲያነቡ እድል ሊሰጧቸው ይገባል። ብዙ ጊዜ ልጆች ሰው ሰጥቷቸው ሳይሆን በራሳቸው መርጠው ማንበብ ይፈልጋሉ። ከዚህ አንፃር ወላጆች ልጆቻቸው ትክክለኛውን የማንበብ ደረጃ ወይም ርእሰ ጉዳይ ካሳሰባቸው ከመጻሕፍት ክፍሎች ውስጥ እንዲመርጡ እድል መስጠት ያስፈልጋል።

**6ኛ. እለት በእለት የንባብ አጋጣሚዎች ይፍጠሩ**

ንባብ ጥሩ መፅሃፍ መርጦ ቁጭ ብሎ የማንበብ ጉዳይ ብቻ አይደለም። የእለት ተእለት ሕይወት አንዱ አካል ጭምርም ነው። ስለዚህ ወላጆች በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ልጆች እንዲያነቡ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህ ግን መሆን ያለበት ልጆች እንዳይሰላቻቸው በማድረግ ነው። ለምሳሌ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር በመኪና አልያም በእግር ሲንቀሳቀሱ በመንገድ ላይ የሚያዩቸውን የማስታወቂያ ፅሁፎች ምን እንደሆኑ በመጠየቅና እንዲያነቡ በማድረግ ንባብን እንዲወዱ ማድረግ ይችላሉ።

**7ኛ. የሚወዷቸውን መጻሕፍት ደግመው እንዲያነቧቸው አድርጉ**

እርስዎ አንድን መጻሕፍት ደጋግመው ሲያነቡ ሊሰለችዎት ይችላል። ነገር ግን ልጆች የሚወዱትን መፅሃፍ ደጋግመው ማንበብ ይወዳሉ። ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ ያመለጡዋቸውን ነገሮች በመፅሐፉ ታሪክ ወይም በምስሎቹ ላይ ማየት ይወዳሉ። እንደገና ማንበብ በገጹ ላይ የሚያዩትን ቃል ከሚሰሙት ቃላት ጋር እንዲያገናኙም እድል ይሰጣቸዋል። ውለው አድረው፣ ልጅዎ መጽሐፉን ለእርስዎ ማንበብ ሊጀምርም ይችላሉ።

**8ኛ. ስለንባብ ይወቁ**

መምህር ላይሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን እርሰዎ የልጅዎ የመጀመሪያ አስተማሪ ነዎት። በተለያዩ የዕድሜ ደረጃዎች ምን ምን የማንበብ ችሎታዎች እንደሚጠበቁ ትንሽ ማወቅ የልጅዎን ንባብ ለመደገፍ ይረዳዎታል። ከዚህ አንፃር ልጆች የንባብ ባህል እንዲያዳብሩ ከተፈለገ ወላጆች ስለንባብ የተወሰነ ፍንጭ ሊኖራቸው ይገባል፤ ማንበብም ይጠበቅባቸዋል።

# ስፖርት





## የአውሮፓ እግር ኳስ የተጨዋቾች ዘዋሪ

**ቦጋለ አበበ**

የፊፋ የተጫዋቾች የዝውውር መስኮት በተከፈተ ቁጥር የታላላቆቹ አውሮፓ ክለቦች ገበያ ሁሌም የስፖርት ቤተሰቡን ቀልብ እንደገዛ ነው። ከዚህ የደራ የተጫዋቾች የዝውውር ገበያ ጀርባ ሆነው የሚዘውሩ ሁለት ሰዎች በዓለም ላይ ገናና ስም ይዘው መነሳታቸው አይቀርም። ሆርጌ ሜንዴዝና ሚኖ ራዮላ።

እነዚህ ስመ ጥር የተጫዋች ወኪሎች በታሪክ የታላላቅ ተጫዋቾች ዝውውር ላይ እጃቸው ማረፉ ብቻ ሳይሆን የአለማችን ከዋክብት ተጫዋቾች እጣ ፋንታ በእጃቸው ላይ መሆኑ በእግር ኳሱ ዓለም ብርቱ ክንድ እንዲኖራቸው አስችሏል። ባለፈው ሳምንት ግን አንዱ ዝነኛና ቱጃር የተጫዋቾች ደላላ ሚኖ ራዮላ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱ ተሰምቷል።

የአውሮፓን እግር ኳስ የሚዘውረው ቱጃር ‘ደላላ’ ማን ነበር? የዛሬው ስፖርት ማህደር አምዳችን ከብዙ በጥቂቱ ዳሶታል። ሚኖ” በተሰኘ ቅፅል ስሙ ይታወቃል፤ የሆላንድና ጣልያን ጥምር ዜግነት ያለው ካርሚን ራዮላ በተጫዋቾች የረጅም አመት የድለላ ሕይወቱ የታዋቂዎቹ ፖል ፖግባ፣ ዝላታን ኢብራሂሞቪች፣ ሄንሪክ ሚኪታሪያንና ዴ ሊት የመሳሰሉ ከዋክብትን የዓለምን ክብረወሰን በሰበረ የዝውውር ገንዘብ ጭምር በመሸጥ ትልቅ ስም ያለው ወኪል ነው።

ይህ እሳት የላሰ ደላላ ጣልያን ተወልዶ በኔዘርላንድስ ሃርለም ከተማ እንዳደገ ይነገርለታል። ከትንሽ ሕይወት ተነስቶ የአለማችንን ውድና ድንቅ ከዋክብት ተጫዋቾች ከትንሽ ተነስተው ትልቅ ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያደረገ ‘ምርጥ ደላላ’ ነው ሲሉም ብዙዎች ይመሰክሩለታል።

ሚኖ በልጅነቱ አባቱ በከፈቱት ሬስቶራንት ውስጥ



**ዝነኛው የእግር ኳስ ተጫዋቾች ደላላ ሚኖ ራዮላ በ54 አመቱ ነው ባለፈው ሳምንት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው፤**

ደፋ ቀና ብሎ አስተናግዷል። ጎን ለጎንም የዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን በመከታተል በሕግ መመረቅ ችሏል።

ዛሬ ላይ ዓለም እንዲያውቀውና የታላላቅ ክለቦችና ተጫዋቾችንም እጣ ፋንታ እንዲወስን ወዳደረገው ስራም በሂደት ነው የገባው። ሚኖ ለአንድ የተጫዋቾች ወኪል ድርጅት ተቀጥሮ ይሠራም ጀመር። የመጀመሪያው ሥራ የሆነው ደግሞ ተስፋ የሚጣልባቸውን ታዳጊ ኔዘርላንድስ ተጫዋቾችን ለጣልያኑ ሴሪ ኤ ማሻሻጥ ነበር። ሚኖ በሂደት ተቀጥሮ ይሠራበት የነበረበትን ድርጅት ለቆ የራሱን የውክልና ድርጅት ሊያቋቁም ቻለ።

ጣልያንኛ፣ ጀርመንኛ፣ ስፓኒሽ፣ ፈረንሳይኛ፣ ፓርቱጊዝ፣ ደች እና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፎ መናገሩም የኋላ ኋላ ለድለላ ሕይወቱ ትልቅ ሚና አበርክቶለታል። ገና የ18 ዓመት ለጋ ሳለ በኔዘርላንድስ ውስጥ የሚገኝ አንድ የታዳጊዎች እግር ኳስ ኃላፊ ሆኖ መስራቱም ለስኬታማ የድለላ ስራው ትልቅ ፋይዳ ነበረው።

በታዳጊነታቸው በሚኖ ደላይነት ወደ ጣልያን ብሎም ወደ እንግሊዝ ክለቦች አቅንተው ስማቸውን በጉልህ መፃፍ ከቻሉ ተጫዋቾች መካከል የቀድሞው የአርሰናል ታሪካዊ ተጫዋች ዴኒስ ቤርግካምፕ ሳይጠቀስ አይታለፍም። በቼክ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ቡድን ባሳየው ድንቅ ብቃት የአውሮፓ ታላላቅ ክለቦች ዓይን አርፎበት የነበረው ፓቬል ኔድቬድ ከስፓርታ ፕራግ ወደ ላዚዮ እንዲዛወር በማድረግም ሚኖ ይታወሳል። አሁን ላይ አውሮፓ ውስጥ ከሚጫወቱ ተጫዋቾች ትልልቅ ስም ያላቸው ከሃያ በላይ ኮከቦች ውክልናቸው የሚኖ ሚኖ ነው።

ሚኖ እኤአ 2016 ላይ የሰራው ታሪክ በብዙዎች ዘንድ ዛሬም ድረስ ይታወሳል። በወቅቱ የዓለም ክብረወሰን በነበረ ዋጋ ፖል ፖግባን ከዩቬንቱስ ወደ ማንችስተር ዩናይትድ እንዲዛወር ያደረገ ሲሆን ዋጋውም 105 ሚሊዮን ዩሮ ነበር። ሚኖም ከዚህ ዝውውር 25 ሚሊዮን ዩሮ በላይ ወደ ኪሱ እንዳስገባ ይነገራል። እኤአ 2017 ላይ ሮሜሉ ሉካኩ ከኤቨርተን ወደ ማንችስተር ዩናይትድ በ75 ሚሊዮን ፓዎንድ፣ እኤአ 2019 ላይ ማቲያስ ዲ ላይት ከአያክስ ወደ ጁቬንቱስ በ67 ነጥብ 5 ሚሊዮን ፓዎንድ የፈረሙበት ታሪክ በሚኖ የድለላ ዘመን ዝነኞቹ ናቸው።

ታላላቆቹን የአውሮፓ ክለቦች በስሙ ብቻ የሚያስደነብረው ሚኖ፣ የሚኖ ስም በእርሱ ውክልና ሥር ያሉ ተጫዋቾችን እንዳሻው ማዟዟር መቻሉ ትልቅ ሀይል ሆኖታል። ይህም ያሻውን ከመናገር ወደኋላ የማይል አድርጎታል። “አትንኩኝ” ባይ መሆኑ የሚነገርለት ሚኖ በእርሱ ውክልና ሥር ያሉ ተጫዋቾችን የሚተቹ የቀድሞ እግር ኳስ ኮከቦችም ሆኑ ተንታኞችን በመወረፍ ይታወቃል።

በአንድ ወቅት ሚኖ በጣልያን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ከውክልና ሥራ መታገዱን ተከትሎ ፊፋም የጣልያን አቻውን ፈለግ በመከተል ራዮላ ላልተወሰነ ጊዜ ከወኪልነት ሥራው እንዲታገድ ውሳኔ አስተላልፎ ነበር። የጣልያን እግር ኳስ ፌዴሬሽን ይህን ውሳኔ ለምን እንዳስተላለፈ ግልፅ ያልነበረ ቢሆንም ሚኖ «እገዳው ብርቅ አልሆነብኝም። እኔ ያልተመቸኝ ውሳኔው ፖለቲካዊ መሆኑ ነው» ሲል ተደምጧል። አክሎም «የጣልያን እግር ኳስ ፌዴሬሽን የአገሪቱን ኳስ ወደኋላ አስቀርቷል ብዬ የተናገርኩት ነገር ሳትቆረቁራቸው አልቀረችም፤ በአገሪቱ ስላለው የእግር ኳስ ዘረኝነት ጉዳይ አሳስቦኛል ማለቴም ይቅርታ ሳያስነፍገኝ አይቀርም» ሲል መሳለቁ ይታወሳል።

በወቅቱ ይህ ውሳኔ ያስደሰታቸው ቢኖሩም የሚኖ መታገድ ለአንዳንድ ክለቦች ትልቅ እንቅፋት ፈጥሮ ነበር። ሚኖ እገዳው ተጥሎበት የነበረው የአውሮፓ እግር ኳስ የዝውውር ገበያ በሚደራበት ወቅት መሆኑ በጊዜው ፖል ፖግባን መግዛት ይፈልጋሉ ከሚባሉት ሪያል ማድሪዶች ጀምሮ የአያክስ ወጣቶችን ለመቀራመት የቋመጡ ክለቦች የራስ ምታት ሆኖባቸው ነበር።

ሚኖ እውቅ የተጫዋቾች ወኪሎችን የሚወክለው ‘ፉትቦል ፎረም’ ፕሬዝደንት ነበር። ፎርብስ የተሰኘው የቢዝነስ ጋዜጣ 2018 ላይ ባወጣው ዘገባ ሚኖ ስልሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር አመታዊ የተጣራ ገቢ እንደነበረው አስቀምጧል። በእርሱ ውክልና ሥራ ያሉ ሰባ ተጫዋቾች ብቻ 629 ሚሊዮን ዶላር ሊያወጡ እንደሚችሉም ጠቁሟል።

በሃምሳ አራት አመቱ ባለፈው ሳምንት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ሚኖ፣ ከፖል ፖግባ ዝውውር በኋላ በአሜሪካዋ የባህር ዳርቻ ግዛት ማያሚ ዘጠኝ ሚሊየን ዩሮ በማፍሰስ በገዛው የመኖሪያ መንደር ቅንጡ ሕይወት ይመራ ነበር።